ጌታዬ ሆይ፥ ውስጣዊውንም ውጫዊውንም ሰውነቴን በችሮታዎችህና በፍቅራዊ ደግነትህ ልብስ አልብስልኝ። ለአንተ በሚያስጠላው በማንኛውም ነገር ከመበከልም ጠብቀኝ፤ እኔና ዘመዶቼም አንተን እንድንታዘዝ በጸጋህ እርዳን፤ እኔም ማንኛውንም የክፋት ወይም የርኩሰት ፍላጎት በውስጤ ከሚቀሰቅስ ነገር ሁሉ እንድርቅ እርዳኝ።

አንተ በእውነቱ፥ የመላው የሰው ዘር ጌታ፤ የዚህ ዓለምና የሚቀጥለው ዓለም ባለቤት ነህና። ከአንተ ከሁሉን አዋቂው፥ ከፍጹም ጠቢቡ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

105

አምላኬ ሆይ፤ ስምህ የተወደሰ ይሁን! አቤቱ አንተ የመላው የሰው ዘር ጌታ ሆይ፤ በፍቅሬ ስሜቶች ሁሉ ወደ አንተ ለመመለስ እችል ዘንድ፤ከእውነት የራቁ እምነቶችንና ከንቱ አስተሳሰቦችን ሁሉ ከልቤ ውስጥ እንድታነጻልኝ፥ በአንተ ትእዛዝና የአንተን ፈቃድ በመከተል በመላው ፍጥረት ውስጥ በተናኙት በጸጋህ ልብስ መዓዛዎች፤ በኃያልነትህና በሉዓላዊነትህ ኃይል አማካይነት፤ ከምሕረትህ አድማስ በላይ በአንጸባራቂነት በአበራው በፈቃድህ የቀኑ ኮከብ እማጸንሃለሁ።

አምላኬ ሆይ፤ እኔ አገልጋይህ የአገልጋይህም ልጅ ነኝ! እኔ የጸጋህን እጀታ አጥብቄ ይዤለሁ፤ ፍቅር በተመላበት ምሕረትህ ገመድም ላይ ተንጠላጥያለሁ። ከአንተ ዘንድ የሚገኙትን መልካም ነገሮች አዘዝልኝ፤



ከቸርነትህ ደማናዎችና ከችሮታህ መንግሥተ ሰማይ ከላክኸው ገበታም መግበኝ።

አንተ በእውነቱ፤ የዓለማት ጌታ፤ በመንግሥተ ሰማይ የሚገኙት ሁሉ፤ በምድር ላይ የሚገኙትም ሁሉ አምላክ ነህና።

106

አምላኬ ሆይ፤ በምድርህ ውስጥ ያቀጣጠልከው ምን ዓይነት እሳት እንደሆነ አላውቅም። ድምቀቱን አፈር ሊያደበዝዘው ከቶ አይችልም። ነበልባሉንም ውሀ ሊያጠፋው አይችልም። የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ኃይሉን ለመቋቋም ኃይል አልባ ናቸው። ወደዚህ እሳት የቀረበ፤ የጩኸቱንም ድምጽ የሰማ ቡራኬው ታላቅ ነው።

አምላኬ ሆይ፤ አንዳንዶቹን በሚያጠናክረው ጸጋህ አማካይነት ወደዚያ እሳት ለመቅረብ አስቻልካቸው፤ ሌሎቹን ግን በቀናትህ እጆቻቸው በሠሯቸው ክፉ ሥራዎች ምክንያት ከዚያ ከለከልካቸው። ወደዚያ በፍጥነት የገሰገሰና እዚያ የደረሰ ማንኛውም ሰው፤ በውበትህ ላይ ለማተኮር ባለው ጉጉት፤ በመንገድህ ሕይወቱን ሰጠ፤ ከአንተ ከራስህም በስተቀር ከሌላ ከማንኛውም ነገር ሙሉ በሙሉ በመላቀቅ ወደ አንተ አረገ።

ጌታዬ ሆይ፤ በግርማህ ዙፋን ፊት ከመቅረብ፤ በበርህም ደጃፍ ላይ ከመቆም የከለከሉኝን ግርዶሾች እንድትቀድልኝ፤ በዚህ በፍጥረት ዓለም በሚነደውና በሚንቀለቀለው እሳት እማጸንሃለሁ። ጌታዬ ሆይ፤

በመጽሐፍህ ከላይ የላክኸውን መልካም ነገር ሁሉ እዘዝልኝ፡ ከምሕረትህም ከለላ እንድባረር አታድርገኝ።

አንተ የሚያስደስትህን ለማድረግ ሙሉ ሥልጣን ያለህ ነህና። አንተ በእውነቱ ፍጹም ኃይል የተመላው፥ ከሁሉም በላይ ሊጋሱ ነህ።

107

ከሁሉም በላይ ተወዳጅ የሆንክ ጌታ ሆይ፡ ምስጋና ለአንተ ይሁን! በእምነትህ ጽኑ አድርገኝ፥ ከእነዚያ ቃል ኪዳንህን ካልጣሱት፡ የገዛ ራሳቸውን ከእውነት የራቁ ከንቱ፡ እምነቶችና ጣዖቶች ካልተከተሉትም ጋር እንድቆጠር ፈቃድህ ይሁን። በአንተ ዘንድ የእውነት መቀመጫ ለማግኘት አስችለኝ፡ የምሕረትህን ምልክት አጎናጽፈኝ፥ ከእነዚያም ምንም ፍርሐት ከማይኖርባቸው፥ በኃዘንም ላይ ከማይጣሉት አገልጋዮችህ ጋር እንድቀላቀል አድርገኝ። ጌታዬ ሆይ፡ ለራሴ አትጣለኝ፥ እርሱን የአንተ የራስህ ክስተት የሆነውን ከማወቅ አትንፈገኝ፥ ከእነዚያ ከአንተ ቅዱስ ቅርበት ፊታቸውን ከአዞሩትም ጋር አትቁጠረኝ። አምላኬ ሆይ፡ ከእነዚያ ውበትህን አትኩሮ ማየትን ከታደሉት፡ በዚያም ትልቅ ደስታን የሚደሰቱ፡ በመሆናቸው፡ የዚያን ትንሿን ጊዜ እንኳ፥ በሰማያትና በምድር መንግሥታት ግዛት ወይም በመላው ፍጥረተ ዓለም ከማይለውጡት ጋር ቁጠረኝ። ጌታ ሆይ፡ የምድርህ ሕዝቦች በአሳዛኝ ሁኔታ በተሳሳቱባቸው በእነዚህ ቀናት፡ በእኔ ላይ ምሕረት ይኑርህ፡ አምላኬ ሆይ፡ በአንተ አስተሳሰብ ተገቢ



የሆነውንም ነገር ለግሰኝ። በእውነቱ፡ አንተ ፍጹም ኃይል የተመላው፥ ጸጋ የተመላው፡ በረከት የተመላው፥ ዘለዓለም ይቅር-ባዩ ነህና።

አምላኬ ሆይ፥ ከእነዚያ ጆሮዎቻቸው ከደነቆሩት፥ ዓይኖቻቸው ከታወሩት፥ አንደበቶቻቸው ንግግር አልባ ከሆኑት፥ ልቦቻቸውም መገንዘብ ከተሳናቸው ጋር እንዳልቆጠር ፈቃድህ ይሁን። ጌታ ሆይ፡ ከድንቁርናና ከራስ ወዳድነት ፍላጎት እሳት አድነኝ፡ ወደ ላቀው ምሕረትህም ክልል እንድገባ አድርገኝ፥ ያንን ለሕሩያንህ ያዘዝከውንም አውርድልኝ። የፈለግኸውን ለማድረግ ችሎታ ያለህ ነህና። በእውነቱ፡ አንተ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፥ በገዛ ራሱ ነዋሪው ነህ።

108

አቤቱ፡ እግዚአብሔር አምላኬ ፡ ጌታዬ ሆይ! እኔ ራሴን ከዘሮቼ አላቅቄአለሁ፡ በአንተም አማካይነት በምድር ላይ ከሚኖሩት ሁሉ ነፃ ለመውጣትና በፊትህ ተመስጋኝ የሆነውን ሁሉ ለመቀበል ምንጊዜም ዝግጁ ለመሆን እሻለሁ። ከአንተ በቀር ከማንኛውም ነገር ነፃ የሚያደርገኝን መልካም ነገር ሁሉ ለግሰኝ፡ ወሰን ከሌላቸው ችሮታዎችህም ይበልጥ የተሟላውን ድርሻ ስጠኝ። በእውነቱ፡ አንተ የተትረፈረፈ ጸጋ ጌታ ነህና።

(በሴት የሚደረግ)

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ከሁሉ ነገሮች የማላቀቅን ጽዋ ሙላልኝ፡ በአንተ ውበቶችና ስጦታዎች ጉባኤም ውስጥ አንተን በማፍቀር ወይን-ጠጅ አስደስተኝ። ከክፉ ስሜትና ፍላጎት ወረራዎች ነፃ አውጣኝ፡ የዚህ የሙታን ዓለምን ሰንሰለቶች ከላዬ በጣጥስልኝ፡ በላቀ ሐሴት ወደ ላቀው መንፈሳዊ ዓለም ሳበኝ፡ በሴት አገልጋዮችም መካከል በቅዱስነትህ እስትንፋሶች አድሰኝ።

ጌታ ሆይ፡ ፊቴን በስጦታዎችህ ብርሃኖች አብራልኝ፡ ዓይኖቼን ፍጹም ድል አድራጊ የሆነውን የኃያልነትህን ምልክቶች ብርሃን በማየት እንዲበሩ አድርግልኝ፡ አቤቱ አንተ የዚህ ዓለምና የላይኛው መንግሥት ንጉሥ ሆይ፡ አቤቱ አንተ የሥልጣንና የኃይል ጌታ ሆይ፡ የአንተን ምልክቶችና ስጦታዎች በሰፊው ለማሰራጨት፡ እምነትህን ለማወጅ፥ ትምህርቶችህን ለማስፋፋት፡ ሕግህን ለማገልገል፥ ቃልህንም ከፍ ከፍ ለማድረግ እችል ዘንድ፥ ልቤን ሁሉን ነገሮች በሚያቅፈው ዕውቀትህ ክብር አስደስትልኝ፡ ነፍሴም በነፍስ ላይ አዲስ ሕይወት በሚዘሩት የታላቅ ሐሴት አስደሳች ዜናዎች እንድትደሰት አድርጋት።

አንተ በእውነቱ፡ ኃይል የተመላው፥ ዘላለም ሰጪው፡ ሁሉን ቻዩ፡ ምንም የማይሳነው ነህ።







አቤቱ አንተ የዘላለም ንጉሥ፥ ብሔረሰቦችን ፈጣሪ፡ እያንዳንዱን ፈራሽ አጥንት ገንቢ የሆንከው ሆይ፡ ክብር ለአንተ ይሁን! ከእነዚያ ከአንተ ከራስህ በስተቀር ከሁሉም ሌላ ነገር ራሳቸውን ከአላቀቁት፥ የገዛ ራሳቸውን ወደ አንተ አቅጣጫ ከመለሱት፡ በአንተ በታዘዙት መከራዎች ወደ ስጦታዎችህ አቅጣጫ ከመዞር ካልተገቱት ጋር እንድትቆጥረኝ፥ የሰው ዘርን በመላ ወደ ግርማህና ወደ ክብርህ አድማስ፥ አገልጋዮችህንም ወደ ጸጋህና ወደ ችሮታዎችህ መንበር በጠራህበት ስምህ እለምንሃለሁ።

ጌታዬ ሆይ፡ የቸርነትህን እጄታ አጥብቄ ይዣለሁ፡ በችሮታህም ካባ ዘርፍ ላይ በጽናት ተንጠላጥዬአለሁ። ስለዚህ የአንተን ትዝታ በስተቀር የሌላውን የማንኛውንም ሰው ትዝታ ከውስጤ የሚያነጻውን ከቸርነትህ ደመናዎች እንድትልክልኝና፡ ወደ እርሱ፥ የአንተን ቃል-ኪዳን ያፈረሱት፡ በአንተና በምልክቶችህ ያላመኑት ቅዋሚ ቀስቃሾች ሊቃወሙት ወደተሰለፉበት፥ የመላው የሰው ዘር የስግደት ዓላማ ወደሆነው ለመመለስ እንድታስችለኝ እለምንሃለሁ።

ጌታዬ ሆይ፡ በቀናትህ የልብስህን መዓዛዎች፥ በገጽህ ብርሃን ውበቶች መከሰቻ ጊዜም የግልጸትህን እስትንፋሶች አትንፈገኝ። አንተ የሚያስደስትህን ነገር ለማድረግ ኃይል የተመላህ ነህና። ምንም ነገር የአንተን

ፈቃድ ሊቋቋም፥ ወይንም አንተ በሥልጣንህ የወሰንከውን ሊያስቀር አይችልም።

ከአንተ ከፍጹም ኃያሉ ፥ ከፍጹም ጠቢቡ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

## 111

እርሱ ኃያሉ ፥ ይቅር-ባዩ፥ ሩኅሩኁ ነው!

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! አገልጋዮችህን በሲኦልና በስሕተት አዘቅት ውስጥ ሆነው ትመለከታቸዋለህ፥ አቤቱ አንተ የዓለም ፍላጎት ሆይ፥ የመለኮታዊ መርሖ ብርሃንህ ወዴት ነው? አንተ ረዳተ-ቢስነታቸውንና ደካማነታቸውን ታውቃለህ፥ አንተ የመንግሥተ-ሰማይና የምድር ኃይሎች ሁሉ በመዳፉ ውስጥ የሚገኙት ሆይ፥ የአንተ ኃይል ወዴት ነው?

ጌታ አምላኬ ሆይ፥ ከእነዚያ በመጽሐፍህ ውስጥ የሚገኙትን ትእዛዛትህን ከአከበሩት አንዱ እንድሆን ፈቃድህ ይሆን ዘንድ፥ በፍትራዊ ደግነትህ ብርሃኖች ውበት፥ በዕውቀትህና በጥበብህ ውቅያኖስም መትመም፥ የመንግሥትህን ሕዝቦች በአሳመንክበትም ቃልህ እለምንሃለሁ። ለታማኞችህ፥ ለእነዚያ የመለኮታዊ ዕውቀት ብልጭታን ወይን-ጠጅ ከቸርነትህ ጽዋ በመጠጣት ፍላጎትህን ለመፈጸምና ቃል-ኪዳንህንና አዲሱን ሥርዓትህን ለመጠበቅ ፈጥነው ለተነሡት ያዘዝክላቸውን ለእኔም እዘዝልኝ። አንተ የፈለግኸውን ለማድረግ ኃይል የተመላህ ነህና።



ከአንተ ከሁሉን አዋቂው፥ ከፍጹም ጠቢቡ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

ጌታ ሆይ፥ አቤቱ አንተ የስሞች ሁሉ ጌታ ሆይ፥ በዚህና በወዲያኛው ዓለም የሚያበለጽገኝንና ወደ አንተ የሚያቀርበኝን በቸርነትህ እዘዝልኝ ። ከአንተ፥ ከአንዱ፥ ከኃያሉ፥ ክብር ከተመላው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

## 112

ጌታ ሆይ፥ እርምጃዎቻችንን በመንገድህ ላይ አጠናክርልን፥ ልቦቻችንንም አንተን እንዲታዘዙ አበርታልን። ገጾቻችንን ወደ አንድነትህ ውበት መልስልን፥ ልቦናዎቻችንን በመለኮታዊ አንድነትህ ምልክቶች አስደስትልን። የሕያዋን ሁሉ ህልውና በታላቅነትህ ራዕይ ፊት የውዳሴህን መዝሙር ይዘምር ዘንድ፥ አካሎቻችንን በጸጋህ መጎናጸፊያ አስጊጥልን፥ ከዓይኖቻችንም ላይ የኃጢአተኛነትን ግርዶሽ ገለጥልን፣ የጸጋህንም ጽዋ ስጠን። ጌታ ሆይ፥ የጸሎት ቅዱስ የላቀ ሐሴት - ከቃላትና ከፊደላት ከፍታ በላይ ከፍ ያለ፥ ከክፍለ-ቃልና ከድምጽ ሁኔታም የመጠቀ ጸሎት - ነፍሶቻችንን ይሞላ ዘንድ፥ ሁሉም ነገሮችም በውበትህ ግልጸት ፊት ፍጹም ወደሌለ- ነገር ይለወጡ ዘንድ፥ ምሕረት በተመላበት ቃላትህና በመለኮታዊ ሕያውነትህ ምሥጢር ራስህን ግለጽ።

ጌታ ሆይ! እነዚህ በቃል-ኪዳንህና በአዲሱ ሥርዓትህ ጥብቅና ጠንካራ ሆነው የቆዩ፥ የእምነትህን የጽናት ገመድ አጥብቀው የያዙ፥ በታላቅነትህም ካባ ጠርዝ ላይ የተንጠላጠሉ አገልጋዮችህ ናቸው። ጌታ

ሆይ፡ በጸጋህ እርዳቸው፡ በኃይልህም አጠናክራቸው፡ አንተንም እንዲታዘዙ ሽንጦቻቸውን አበርታ።
አንተ ይቅር-ባዩ፡ ጸጋ የተመላው ነህና።

## 113

አቤቱ አንተ ሩኅሩኅ አምላክ ሆይ! ስለአነቃኸኝና እንዳስተውል ስለአደረግኸኝ ምስጋና ለአንተ ይሁን። የሚያይ ዓይን ሰጠኸኝ፡ የሚሰማ ጆሮም ለገስከኝ፡ ወደ መንግሥትህ እንድገባ አደረግኸኝ፡ ወደ መንገድህም መራኸኝ። ትክክለኛውን መንገድ አሳየኸኝ፡ ወደ መዳኛ መርከብም እንድገባ አደረግኸኝ። አምላክ ሆይ! ጽኑ ፡ ጠንካራና የማልበገር እንድሆን አድርገኝ። ከኃይለኛ ፈተናዎች ጠብቀኝ፡ በኃይል በተጠናከረው የቃል-ኪዳንህና የአዲሱ ሥርዓትህ ምሽግ ውስጥ ከልለህና ጠብቀህ አኑረኝ። አንተ ኃይል የተመላው ነህ። አንተ የሚያየው ነህ። አንተ ሰሚው ነህ።

አቤቱ አንተ ሩኅሩኁ አምላክ ሆይ። እንደመስታወት በፍቅርህ ብርሃን የሚያንጸባርቅ ልብ ስጠኝ፡ ይህን ዓለም በመንፈሳዊ የጸጋ ኅርፎች አማካይነት ወደ ጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ ለመለወጥ የሚያስችሉኝን አስተሳሰቦች ለግሰኝ።

አንተ ሩኅሩኁ፡ መሐሪው ነህ። አንተ ታላቁ ቸር አምላክ ነህ።



## 114

አቤቱ አንተ ጌታዬና አለኝታዬ ሆይ! ተወዳጆችህ በኃያሉ ቃል-ኪዳንህ ጽኑ እንዲሆኑ፥ ለግልጹ እምነትህ ታማኝ ሆነው እንዲኖሩ፡ በብርሃናት መጽሐፍህ ውስጥ ያሰፈርካቸውን ትእዛዛት እንዲፈጽሙ፡ የመርሐ ዓርማዎችና የላይኛው ዓለም ጉባኤ ሩኖሶች፡ ወሰን የሌለው ጥበብህ ምንጮች፥ ከከፍተኛው ሰማይ በማብራት በትክክል የሚመሩ ከዋክብት እንዲሆኑ እርዳቸው።

በእውነቱ፡ አንተ የማይበገረው፡ ፍጹም ኃያሉ፡ ፍጹም ኃይል የተመላው ነህና።

<u>ለቤተሰብ።</u>

## 115

አምላኬ ሆይ፡ አንተ የተመሰገንክ ነህ! ይህ የአንተ አገልጋይ ከአንተ በስተቀር ሌላ ምንም ነገር ስለ አንተ ለመግለጽ እንደማይችል፡ በአንተ በራስህም በስተቀር በሌላ በማንም ሰው ስለ አንተ መግለጫ ሊቀርብ እንደማይችል ይመሠክራል። የእነዚያ የአንተን እውነታ ያወቁት ሰዎች ሃሣቦች አንተን ወደሚወደስ ሰማይ ምንም ያህል የመጠቁ ቢሆኑም እንኳ፡ በአንተ ፈቃድና ትእዛዝ በራሳቸው ልቦች ውስጥ ከተደረጉት ገደቦች ለማለፍ ተስፋ ማድረግ ከቶ አይችሉም። ምንም እንደሌለ ነገር የሆነው ፍጡር እርሱን የቀናት ቀደምቱ የሆነውን እንዴት ሊገነዘብ ይችላል፡ ወይም የእርሱን ሥልጣን፡ የእርሱን ክብር፡

የእርሱንም ታላቅነት ሙሉ መጠን ለመግለጽ የሚያደርገው ሙከራ እንዴት ሊሳካለት ይችላል? የለም አይችልም፥ አቤቱ አንተ የወገኖች ገዢ ሆይ፡ ለዚሁም አንተ ራስህ ትመሠክራለህ! እያንዳንዱ የተፈጠረ ነገር፥ ስለራሱ ኃይል አልባነትና ስለአንተ ኃያልነት ኃይል ተገንዝቧል፥ ስለራሱም የተዋረደ መሆንና ስለ አንተ ታላቅ ክብር አምኗል።

እነዚያ ለአንተ ውድ የሆኑት፡ ልጆቻቸውም፥ ዘመዶቻቸውም በፍጡሮችህ መካከል የንጹህነትህ መገለጫዎች፥ በአገልጋዮችህም መካከል የቅዱስነትህ መከሰቻዎች እንዲሆኑ ፈቃድህ ይሆን ዘንድ፥ ከአንደኛነትህ ጋር አንድ ዓይነት በሆነው መጨረሻነትህ፥ ከሥውርነትህ ጋር አንድ ዓይነት በሆነውም መገለጽህ እማጸንሃለሁ።

በእውነቱ፥ አንተ የሚያስደስትህን ለማድረግ ሙሉ ሥልጣን ያለህ ነህና። በእርግጥም፡ አንተ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፥ በገዛ ራሱም ነዋሪው ነህ።

## 116

ጌታ አምላኬ ሆይ፥ ክብር ለአንተ ይሁን! እኔንና እነዚያን እምነትህን የሚደግፉትን ይቅር እንድትለን እለምንሃለሁ። በእውነቱ አንተ የላቀው ጌታ፥ ይቅር-ባዩ፥ ከሁሉም በላይ ቸሩ ነህና። አምላኬ ሆይ! እነዚያን ዕውቀት የተነፈጉትን አገልጋዮችህን ወደ እምነትህ ለመግባት አስችላቸው፤ አንዴ ስለ አንተ ቢያውቁ፥ ስለፍርድ ቀን ይመሠክራሉና፥ የቸርነትህንም መገለጽ አያስተባብሉምና። የጸጋህን ምልክቶች ላክላቸው፥



በሚኖሩበትም ቦታ ሁሉ፡ ያንን ከአገልጋዮችህ መካከል ለሃይማኖተኞቹ ያዘዝከውን ስፉ ድርሻ ፍቀድላቸው። አንተ በእውነቱ የላቀው ገዢ፥ ፍጹም በረከት የተመላው፡ ከሁሉም በላይ ቸሩ ነህና።

አምላኬ ሆይ! ለጸጋህ መገለጫና ከአንተ ዘንድ ለፍቅራዊ ደግነትህ ምልክት እንዲሆኑ፡ የጸጋህና የቡራኬዎችህ ዶፎች፥ ነዋሪዎቻቸው እምነትህን በተቀበሉት ቤቶች ላይ እንዲወርዱ አድርግ። በእውነቱ አንተ ይቅርታ በማድረግ የማይደረስብህ ነህና። ከማንም ሰው የአንተ ጸጋ ቢከለከል፡ በቀንህ እምነትህን ከሚከተሉት መካከል ሊቆጠር እንዴት ይችላል?

አምላኬ ሆይ፥ እኔን፡ እነዚያንም በተወሰነው ቀን በምልክቶችህ የሚያምኑትን፡ እነዚያን፡ ለእኔ ፍቅር፡ አንተ በውስጣቸው ለምታሰርጽባቸው ፍቅር በልቦቻቸው ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ለሰጡትም ቡራኬ እንድትሰጠን እለምንሃለሁ። በእውነቱ አንተ የጽድቅ ጌታ፡ ከሁሉም በላይ የተከበረው ነህና።

## 117

አምላኬ ሆይ፡ ይቅር ባይነትህን እለምናለሁ፡ አገልጋዮችህ ራሳቸውን ወደ አንተ እንዲያመሩ በምትፈልግበት ሁኔታም ይቅርታህን እማጸናለሁ። ለጌታነትህ እንደሚገባው ኃጢአቶቻችንን ከእኛ ላይ እንድታነፃ፥ እኔን፡ ወላጆቼን፡ እነዚያንም በአንተ አስተሳሰብ ከሁሉ በላይ ለሆነው ለዓላዊነትህና

ለመንግሥተ ሰማያዊው ኃይልህ ክብር በሚገባው ሁኔታ፡ ወደ ፍቅርህ መኖሪያ የገቡትን ይቅር እንድትለን እለምንሃለሁ።

አምላኬ ሆይ! አንተ ነፍሴ ልመናዋን ለአንተ እንድታቀርብ አነቃቅተሃታል፡ አንተ ባታነቃቃት ኖሮ፡ ባልለመንኩህ ነበር። የተመሰገንህና የተከበርክ ነህ፡ ራስህን ስለገለጽህልኝ ምስጋና አቀርብልሃለሁ፡ አንተን የማወቅ ተግባሬን ስለአሟላልኩና በፍቅርህም መንገድ ባለመራመዴ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ።

## 118

ጌታ አምላካችን ሆይ፡ ስምህ የተመሰገነ ይሁን! በእውነት፤ አንተ የማይታዩትን ነገሮች ሁሉ አዋቂው ነህ። ሁሉን የሚያቅፍ ዕውቀትህ ሊለካው የማይችለውን ዓይነት መልካም ነገር እዘዝልን። አንተ የላቀው ጌታ፡ ፍጹም ኃያሉ፡ ፍጹም ተወዳጁ ነህና።

ጌታ ሆይ፡ ምስጋና ሁሉ ለአንተ ይሁን! ቀጠሮ በተወሰነለት ቀን ጺጋህን እንሻለን፡ እምነታችንንም ጌታችን በሆንከው በአንተ ላይ እናደርጋለን። አምላክ ሆይ፡ ከአንተ በስተቀር ሌላውን ነገር ሁሉ ለመተው እንድንችል መልካሙንና ተገቢ የሆነውን ስጠን። በእውነት፤ አንተ የዓለማት ሁሉ ጌታ ነህና።

አምላክ ሆይ! እነዚያን በቀናትህ በትዕግሥት ችለው የሚኖሩትን ካማቸው፡ ከመንገድም ሳይወጡ በእውነት መንገድ እንዲራመዱ ልቦቻቸውን አበርታ። ጌታ ሆይ! ሐሴት ወደተመላበት ገነትህ መግባትን ለማግኘት የሚያስችሉአቸውን አስደሳች ስጦታዎች



አድላቸው። ጌታ አምላክ ሆይ፡ አንተ የተከበርክ ነህ። የመንግሥተ ሰማይ የሆኑት ቡራኬዎችህ ነዋሪዎቻቸው በአንተ በአመኑብህ ቤቶች ላይ እንዲወርዱ አድርግ። በእውነት፤ መለኮታዊ ቡራኬዎችን በማውረድ የሚወዳደርህ የለምና። አምላክ ሆይ፡ ታማኝ አገልጋዮችህን ድል አድራጊዎች የሚያደርጉአቸውን ሠራዊቶች ስደድላቸው። አንተ የተፈጠሩትን ነገሮች በትእዛዝህ ኃይል እንደፈለግህ ታደርጋቸዋለህ። በእውነት፤ አንተ የላቀው ገዢ ፡ ፈጣሪው፡ ፍጹም ጠቢቡ ነህና።

በል፡- በእውነት፤ አምላክ ሁሉን ነገሮች ሠሪው ነው። እርሱ ለሕይወት አስፈላጊ የሆነውን ነገር ለፈቀደው ለማንኛውም ሰው በገፍ ይሰጣል። እርሱ ፈጣሪው፡ የሕያዋን ሁሉ ምንጭ፡ የሚያበጀው፡ ፍጹም ኃያሉ ፡ ሠሪው፡ ፍጹም ጠቢቡ ነው። እርሱ በሰማያትና በምድር፡ በመካከላቸውም በሚገኘው ሁሉ ውስጥ ከሁሉም በላይ የላቁ ስያሜዎችን የተጎናጸፈው ነው። ሁሉ ትእዛዙን ይፈጽማሉ፡ የምድርና የሰማይ ነዋሪዎችም ለእርሱ ምስጋና ያቀርባሉ፡ ሁሉም ወደ እርሱ ይመለሳሉ።

## 119

አቤቱ፤ ጌታ ሆይ! በዚህ ከሁሉም በላይ ታላቅ በሆነው የግልጸት ዘመን ልጆች ለወላጆቻቸው የሚማለዱላቸውን ምልጃ ትቀበላለህ። ይህም ለዚህ ግልጸት ዘመን ከተሰጡት ወሰን ከሌላቸው ልዩ ስጦታዎች መካከል አንዱ ነው። ስለዚህም፡ አቤቱ፤

አንተ ሩኅሩኅ ጌታ ሆይ፡ ይህ በአንድዬነትህ ደጅስላም አገልጋይህ የሆነው የሚያቀርበውን ልመና ተቀብለህ አባቱን በጸጋህ ውቅያኖስ ውስጥ አስጥመው፡ ምክንያቱም ይህ ልጅ ለአንተ አገልግሎት ለመስጠት ተነሥቷልና፡ በሁሉ ጊዜያትም በፍቅርህ መንገድ ጥረት በማድረግ ላይ ነውና:: በእውነት፡ አንተ ሰጪው፡ ይቅር-ባዩ፡ ሩኅሩኁ ነህ::

120

(በሴት የሚደረግ)

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ይህቺ አገልጋይህ ፡ መንግሥተ ሰማያዊ ችሮታዎችህን እንድታዘንብባት፡ መንፈሳዊ ምሥጢራትህንም እንድትገልጽላት፡ የአምላክነትህንም ብርሃኖች በላይዋ እንድታበራ እምነቷን በአንተ ላይ በመጣልና ፊቷን ወደ አንተ በመመለስ፡ አንተን በመማጸን፡ ወደ አንተ በመጣራት ላይ ናት::

ጌታዬ ሆይ! የባለቤቱ ዓይኖች እንዲያዩ አድርጋቸው:: ልቡ አንተን በማወቅ ብርሃን ሐሴት እንዲያደርግ አድርገው፡ አዕምሮውንም ወደ እንጸባራቂው ውበትህ ሳበው፡ ግልጽ ብርሃኖችህን ለእርሱ በመግለጽ መንፈሱን አስደስትለት::

ጌታዬ ሆይ! ግርዶሹን ከዓይኑ ፊት አንሣለት:: የተትረፈረፉ ችሮታዎችህን በላዩ አዘንብለት፡ አንተን በማፍቀር ወይን ጠጅ አስክረው፡ ልክ ነፍሶቻቸው ከፍ ባሉት ሰማያት ውስጥ እንደሚከንፉ ሁሉ፡ እግሮቻቸው በዚህ ምድር ላይ ከሚራመዱት መላእክት መካከል



እንዱ አድርገው:: በሕዝብህ መካከል በጥበብህ ብርሃን የሚያበራ ብሩህ ፋኖስ እንዲሆን አድርገው::

በእውነቱ፡ አንተ ክቡሩ፡ ዘላለም ሰጪው፡ የመስጠት እጁ ምንጊዜም የተዘረጋው ነህና::

121

(በነፍስ ጡር የሚደረግ)

ጌታዬ ሆይ! ጌታዬ ሆይ! በእውነቱ ወደ ግልጹ መንግሥትህ ስለመራሃት፡ በአላፊ ጠፊውም ዓለም የአንተን ጥሪ እንድትሰማና በሁሉም ነገሮች ውስጥ የአንተን ድል አድራጊ ንግሥና መከሰት የሚያረጋግጡትን ምልክቶችህን ለማየት እንድትችል ስላደረግሃት ለምትለምንህና ለምትማጸንህ ባሪያህ፡ ለትሑቷ ሴት አገልጋይህ ለለገስካት ችሮታ አወድስሃለሁ፡ ደግሜም አመሰግንሃለሁ::

ጌታዬ ሆይ! ይህን በማሕጸኔ ውስጥ ያለውን ለአንተ አደራ ሰጥቻለሁ:: ስለዚህ በአንተ ችሮታና ቸርነት፡ በመንግሥትህ ውስጥ ተመስጋኝ ሕፃንና የታደለ ነፍስ ይሆን ዘንድ፡ በአንተ ትምህርት ጥበቃ ሥር እንዲያድግና እንዲዳብር አድርገው:: በእውነቱ አንተ ጸጋ የተመላው ነህ! በእርግጥ፡ አንተ የታላቅ ችሮታ ጌታ ነህ!

## የእግዚአብሔር እምነት እደ ሃይማኖቶች

*"… የባሃኦላህ ቃል ኪዳን ማዕከል (የአብዱል ባሃ) የማይሳሳት ብዕር የአባቱን እምነት ደህንነት የመጠበቅንና መስፋፋቱን የማረጋገጥን ሁለት ተግባራት ያጎናጸፉቸው፡ በሁቃየት ደረጃ ላይ ያለው የባሃኦላህ የዓለም የጋራ ሀብት ማኅበረሰብ ዋንኛቹ ተንከባካቢዎች፡፡"*

## ለእደ ሃይማኖቶች የሚደረግ ጸሎት

122

በእነርሱ አማካይነት የማይበገር ጽናት ብርሃን በአበራውና የመምረጥ ሥልጣን ኃይል የተመላው፡ የኃያሉ፡ የማይገታው አምላክ የመሆኑ እውነትነት በተረጋገጠው፡ በእነርሱ አማካይነት የጸጋ ውቅያኖስ በተመመውና የሰው ዘር ጌታ የሆነው አምላክ ጸጋ የተመላባቸው ችሮታዎች መዓዛ በአረበበው፡ በእግዚአብሔር እምነት እደ ሃይማኖቶች ላይ ብርሃንና ክብር፡ ሰላምታና ምስጋና ይሁን፡፡ እርሱ የተከበረ ነውና ፡ በሠራዊቶቹ አማካይነት እንዲከላከልላቸው፡ በሁሉን ቻይ ሥልጣኑ እንዲጠብቃቸው፡ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ላይ ድል አድራጊ በሆነው በማይሸነፈው ኃይሉም እንዲረዳቸው እርሱን እንማጸናለን፡፡ ሥልጣን የሰማያት ፈጣሪና የስሞች ዓለም ጌታ የሆነው የእግዚአብሔር ነው፡፡



## ለ) የግዴታ ጸሎቶች

*"ስለታዊ የግዴታ ጸሎቶች በቁጥር ሦስት ናቸው፡፡… ምዕመኑ ከእነዚህ ከሦስቱ ጸሎቶች የፈለገውን አንዱን ለመምረጥ ሙሉ በሙሉ ነፃ ነው፤ ግን ከእነዚህ አንዱን አብረውት በሚሄዱት መመሪያዎች መሠረት የመድገም ግዴታ አለበት፡፡"*

*"የግዴታ ጸሎቶች ትሕትናንና ታዛዥነትን የሚጋብዙና፡ ሰው ፊቱን ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ለእርሱ ምህላ እንዲያቀርብ የሚረዱት በመሆናቸው፡በየዕለቱ መደገማቸው ግዴታ ነው፡፡ እንዲህ ባሉት ጸሎቶችም አማካይነት የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፡ ወደ እርሱም ለመቅረብ ይሻል፡ ከእውነተኛ የልቡ ፍቅረኛም ጋር ይነጋገራል፡ እንዲሁም መንፈሳዊ ደረጃዎችን ይቀዳጃል፡፡"*

### አጭሩ ፡-

123

ይህ ጸሎት በየዕለቱ ከቀትር እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ባለው ጊዜ ውስጥ አንዴ የሚደረግ ነው፡፡

አምላኬ ሆይ፦ አንተን እንዳውቅና እንድሰግድልህ እንደፈጠርከኝ እመሰክራለሁ፡፡ በዚህች ሰዓት የእኔን ደካማነትና የአንተን ኃያልነት፦የእኔን ምስኪንነትና የአንተን ሀብታምነት አረጋግጣለሁ፡፡

ከአንተ በአደጋ ጊዜ ረዳት፡ በገዛ ራሱም ነዋሪ ከሆንከው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡

**መካከለኛው:-**

124

በየሰላቱ ጊዜ፦ እኩለ ቀንና ማታ የሚደረግ:: ለመጸለይ የሚሻ ሁሉ እጁን ይታጠብ፤ በመታጠብም ላይ ሳለ እንዲህ ይበል:-

አምላኬ ሆይ፡ መጽሐፍህን አጥብቆ እንዲይዝና የዓለምም አጀቦች በላዩ ላይ ኃይል እንዳይኖራቸው፡ እጄን አበርታ:: የእርሱም ባልሆነው በማንኛውም ነገር ውስጥ እንዳይገባ ጠብቀው:: በእውነቱ አንተ ፍጹም ኃያሉ፡ ከሁሉ በላይ ኃይል የተመላው ነህና::

ቀጥሎ ፊቱን በመታጠብ ላይ እያለ እንዲህ ይበል:-

ጌታዬ ሆይ፡ ፊቴን ወደ አንተ መልሻለሁ! በገጽህ ብርሃን አብራው:: ወደ አንተም በቀር ወደ ማንም እንዳይዞር ጠብቀው::

ከዚያም ይቁም፡ ፊቱን ወደ ቂብለ.ህ "የሙዳሴ ማዕከል፡ ማለትም ወደ ባሕጂ፡ አቃር" በመመለስ እንዲህ ይበል:-

ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ራሱ ይመሰክራል:: የግልጽነትና የፍጥረት መንግሥታት የእርሱ ናቸው:: እርሱ በእውነቱ የግልጸት ጎሕ የሆነውን፡ በሲና ላይ የተነጋገረውን፥ በእርሱም አማካይነት የላቀው አድማስ እንዲያበራ የተደረገውን፡ በእርሱም ሊታለፍ የማይቻለው የሎጥ ዛፍ የተናገረውን ፡ በእርሱም አማካይነት በሰማይና በምድር ላሉት ሁሉ:- *"እነሆ፡ የሁሉ ባለቤት የሆነው*



*መጥቷል:: ምድርና ሰማይ፡ ከተማና ግዛት፡ የሰዎች ሁሉ ጌታ፡ የላይኛውና የምድሩ ሁሉን ባለቤት የሆነው የአምላክ ናቸው!"* የሚለው ጥሪ የታወጀበትን ከስቶታል::

ከዚያም ያጎንብስና እጆቹን በጉልበቶቹ ላይ በማሳረፍ እንዲህ ይበል:-

አንተ ከእኔ ሙገሳና ከማንም ሰው ሙገሳ በላይ፡ ከእኔ ገለጻና በሰማይና በምድር ካሉት ሁሉ ገለጻ በላይ የተከበርክ ነህ::

ከዚያም ቆሞ እጆቹን በመዘርጋት መዳፎቹንም ወደላይና ወደፊት በማቅናት እንዲህ ይበል:-

አምላኬ ሆይ፡ እርሱን በተማጸኝ ጣቶቹ፡ በምሕረትህና በጸጋህ ዘርፍ ላይ የተንጠላጠለውን ቅር አታሰኘው፤ አቤቱ አንተ ምሕረትን ከሚያሳዩ ሁሉ ፍጹም መሐሪው ነህና!

ከዚያም ይቀመጥና እንዲህ ይበል:-

አንድነትህንና አንድዬነትህን፡ አንተ አምላክ መሆንህን፥ ከአንተም በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ:: በእውነቱ አንተ እምነትህን ገልጸሃል፥ ቃል-ኪዳንህንም አሟልተሃል፥ በሰማይ ውስጥና በምድር ላይ ለሚኖሩትም ሁሉ የጸጋህን በር በሰፊው ከፍተሃል:: የዓለም ለውጦችና አጋጣሚዎች ወደ አንተ ከመመለስ ሊያደናቅፉአቸው ያልቻሉ፡ እና በአንተ ዘንድ ያለውን ለማግኘት ተስፋ በማድረግ፥ ያላቸውን

ሁሉ በሰውት በተወዳጆችህ ላይ ቡራኬና ሰላም፡ ሰላምታና ክብር ይረፍ:: በእውነቱ አንተ ምንጊዜም ይቅር-ባዩ፡ ፍጹም ጸጋ የተመላው ነህና::

ረጅሙ::

125

በሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ አንዴ የሚደገረማ:: ይህን ጸሎት ለመድገም የሚሻ ይቁምና ልቡናውን ወደ እግዚአብሔር ያቅና፡ በሥፍራውም እንደቆመ የሩጎሩጉን፡ የይቅር-ባዩን አምላክ ምሕረት እንደሚጠባበቅ ሁሉ ወደ ቀኝና ወደ ግራ ይመልከት:: ከዚያም እንዲህ ይበል፡

አቤቱ አንተ የስሞች ሁሉ ጌታና የሰማየት ፈጣሪ የሆንከው ሆይ! ጸሎቱ፥ ውበትህን እንዳላይ የጋረደኝን ግርዶሽ የሚያነድ እሳትና፡ ወደ ሕልውናህም ውቅያኖስ የሚመራኝ ብርሃን እንዲሆን፡ በእነዚያ፥ ፍጹም የተከበረው፡ የንፁዱና ሊታይ የማይቻለው የአንተ ሕልውና ኀሕ በሆኑት እማጸንሃለሁ::

ቀጥሎም ፡እግዚአብሔር የተባረከና የተከበረ ይሁንና፡ እጆቹን ወደ እርሱ በልመና በማንሳት እንዲህ ይበል::

አቤቱ አንተ የዓለም እሾትና የብሔሮች ሁሉ ተወዳጅ የሆንከው ሆይ! ወደ አንተ ዞሬ፥ ከአንተ በቀር ከማንኛውም ቁራኛነት ሁሉ ተላቅቄ በእንቅስቃሴው መላው ፍጥረት በተቀሰቀሰበት ገመድህ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ:: ጌታዬ ሆይ፥ እኔ አገልጋይህ የአገልጋይህም ልጅ ነኝ:: ፈቃድንህና ፍላጎትህን ለመፈጸም ዝግጁ ሆኜ መቆሜንና ከበጎ ፈቃድህም



በስተቀር ሌላ እንደማልሻ ተመልከተኝ:: አገልጋይህን እንደፈቀድከውና እንዳሻህ እንድታደርገው በምሕረትህ ውቅያኖስና በጸጋህ የቀኑ ኮከብ (የዘመኑ ፀሐይ) እማጠንሃለሁ:: ከመነገርና ከመወደስ በላይ በጣም ከፍ ባለው ኀያልነትህ! በአንተ የተገለጸ ማንኛውም ነገር የልቤ ፍላጎትና የነፍሴ ተወዳጅ ነው:: እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ሰማየትንና ምድርን የከበበውን ፈቃድህን ተመልከት እንጂ ፡ ምኞቶቼንና አድራጎቶቼን አትመልከት:: በፍጹም ታላቁ ስምህ፡ አቤቱ አንተ የብሔሮች ሁሉ ጌታ ሆይ! አንተ የፈለግኸውን ብቻ ፈልጌአለሁ፥ የምታፈቅረውንም ብቻ አፈቅራለሁ::

ከዚያም በኋላ ተንበርክኮ ግንባሩን ወደ መሬት በመድፋት እንዲህ ይበል፡

ከራስህ ገለጻ በቀር ከማንም ገለጻ፥ ከአንተም የመረዳት ችሎታ በቀር ከማንም የመረዳት ችሎታ በላይ የላቅህ ነህ::

ቀጥሎም ይቁምና እንዲህ ይበል፡

ጌታዬ ሆይ ፡ ጸሎቴን ፡ ለዓላዊነትህ እስካለ ድረስ ለመኖርና በዓለማትህም እያንዳንዱ ዓለም ስምህን ላወሳበት የምችልበት፡ የሕይወት ውሀዎች ምንጭ አድርግልኝ::

እንደገና በመቆጸን እጆቹን ወደላይ በማንሣት እንዲህ ይበል፡

አቤቱ ከአንተ ሲለዩ ልቦችና ነፍሶች የቀለጡ፡ በፍቅርህም እሳት መላው ዓለም የተቀጣጠለው ሆይ! አቤቱ አንተ በሰዎች ሁሉ ላይ ገዥ የሆንከው ሆይ! በአንተ ዘንድ የሚገኘውን እንዳትነፍገኝ ፡ መላውን ፍጥረት ባንበረከክህበት ስምህ እማጠንሃለሁ። ጌታዬ ሆይ፡ ይህ ባይተዋር በግርማህ ከለላ ሥር፡ በምሕረትህ ክልል ውስጥ ወዳለው፡ እጅግ በጣም ወደ ተከበረው ቤቱ ሲገሰግሥ ፡ ይህ ኃጢአተኛ የይቅር ባይነትህን ውቅያኖስ፡ ይህ ዝቅተኛ የክብርህን መንበር ፡ ይህ ምስኪን ፍጡር የሀብትህን ምንጭ ሲሻ ትመለከታለህ። የፈቀድከውን ማንኛውንም ነገር የማዘዝ ሥልጣን ያንተ ነው። በሥራዎችህ መመስገን፡ ለትእዛዞችህም ታዛዥነትን ማግኘት፡ ትእዛዝ በመስጠትም ገደብ የሌለብህ ሆነህ ጸንተህ የምትኖር መሆንህን እመሰክራለሁ።

ቀጥሎም እጆቹን ወደላይ በማንሣት ከሁሉ በላይ ታላቁን ስም፡ ማለትም "አላሁ አ አብሃ" (አምላክ ፍጹም ክቡር) የሚለውን ሦስት ጊዜ ይደጋግም። አምላክ ይክበር ይመስገንና በእርሱ ፊት አጎንብሶ እጆቹን ጉልበቶቹ ላይ በማሳረፍ እንዲህ ይበል፡

አምላኬ ሆይ፡ አንተን ለማምለክ በመናፈቁ፡ አንተን ለማስታወስና ለማሞገስ በጣም በመመኘቱ መንፈሴ በመላው አካላቴ ውስጥ እንዴት እንደተንቀሳቀሰ፡ ለዚያ በቃልህ መንግሥትና በዕውቀትህ ሰማይ የትእዛዝህ ልሳን ለመመስከረለትም መንፈሴ እንዴት እንደሚመሰክር ታያለህ። አቤቱ



ጌታዬ ፡ በዚህ ሁኔታ የእኔን ምስኪንነት እንዳሳይና የአንተን በረከቶችና ጸጋዎች እንዳወሳ፡ የእኔን ደካማነት እንድመሰክርና የአንተን ሥልጣንና ኃያልነት እንድገልጽ፡ ከአንተ ጋር ያለውን ሁሉ ከአንተ መለመን እወዳለሁ።

ቀጥሎም ይቁም፡በመቆጸንም እጆቹን ሁለቴ ወደ ላይ ያንሳና እንዲህ ይበል፡-

ከአንተ ከፍጹም ኃያሉ፡ ከፍጹም ለጋሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። በመጀመሪያም ሆነ በመጨረሻ ሁሉን ደንጋጊ ከሆንከው፡ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም። እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ይቅርታህ ድፍረትን ሰጥቶኛል፡ ምሕረትህ አጠንክሮኛል፡ ጥሪህ ቀስቅሶኛል፡ ጸጋህም አስነስቶ ወደ አንተ መርቶኛል። እንግዲያውማ በቅርበትህ ከተማ በር ላይ ልቆም ፡ ወይም ከፈቃድህ ሰማይ ወደሚያበሩት ብርሃናት ፊቴን ለመመለስ የምደፍር እኔ ማን ነኝ? ጌታዬ ሆይ፡ ይህ ጎስቋላ ፍጡር የጸጋህን በር ሲያንኳኳ፡ ይህ ኢምንት ነፍስ ከበረከትህ እጆች ዘለዓለማዊውን የሕይወት ጅረት ሲሻ ትመለከታለህ። አቤቱ አንተ የስሞች ሁሉ ጌታ ሆይ፡ ትእዛዝ ምንጊዜም ያንተው ነው፡ አቤቱ የሰማያት ፈጣሪ ሆይ፡ የእኔ ግን ሁሉንም መተውና ለፈቃድህ በውዴታ መገዛት ነው።

ቀጥሎም እጆቹን ሦስቴ ወደ ላይ በማንሣት እንዲህ ይበል፦

እግዚአብሔር ከታላቅ ሁሉ ይበልጥ ታላቅ ነው።

ቀጥሎም ተምበርክኮ ግምባሩን ወደ መሬት በመድፋት እንዲህ ይበል፦

ወደ አንተ የቀረቡት የሚያቀርቡት ምስጋና ወደ ቅርበትህ ሰማይ ከመውጣት፤ ወይም የእነዚያ ለአንተ ያደሩት ሰዎች ልቦች አዕዋፋት ወደ መንበርህ በር ከመድረስ በጣም ከፍ ያልክ ነህ። አንተ ከባሕርያት ሁሉ የነጻህ፤ ከስሞችም ሁሉ በላይ ቅዱስ መሆንህን እመሠክራለሁ። ከአንተ ፍጹም ከላቀው፥ ከንዑዱ በቀር ሌላ አምላክ የለም።

ቀጥሎም ይቀመጥና እንዲህ ይበል፦

የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ፥ የሰማይ ሠራዊት፤ የገነተ አርያም ነዋሪዎች፥ ከእነዚህም በላይ ከፍጹም ደማቁ አድማስ የታላቁ አንደበት ራሱም የሚመሠክሩልህ፤ አንተ አምላክ መሆንህንና ከአንተም በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ፤ እርሱም ያ የተከሰተው፤ በእርሱም አማካይነት ሁ እና ን (ሁን) ፊደላት የተገናኙበትና የተጣመሩበት፥ ሥውሩ ምሥጢር ፡ ብርቱ ምልክት መሆኑን እመሠክራለሁ። ስሙ ከሁሉም በላይ ከፍተኛ በሆነው ብዕር የሠፈረው፥ በአምላክ መጻሕፍትም ውስጥ የተጠቀሰው፥ የሰማይና የምድር ዙፋን ጌታ እርሱ መሆኑን እመሠክራለሁ።



ቀጥሎም ቀጥ ብሎ ይቁምና እንዲህ ይበል፡

አቤቱ የፍጡራን ሁሉ ጌታና የሚታዩትም የማይታዩትም ነገሮች ሁሉ ባለቤት ሆይ! አንተ አምባዬንና የማሰማውን ሲቃ እነሆ ታስተውላለህ ፤ የማቃስቴን ድምፅ፤ ዋይታዬን ፤ የልቤንም ስቆቃ ትሰማለህ። በኀያልነትህ ! ሕግ ተላላፊነቴ ወደ አንተ ከመቅረብ አግዶኛል ፤ ኃጢአቴም ከቅድስናህ መንበር አግልሎኛል። አቤቱ ጌታዬ፤ ፍቅርህ አበልጽጎኛል፤ ከአንተም መለየት አጥፍቶኛል፤ ከአንተ መራቅም ጨርሶኛል። በውበትህ ላይ ለማተኮርና በመጽሐፍህ ውስጥ ያሉትን ሁሉ ለማክበር እንድችል እንድትወስንልኝ ፤ በዚህ ምድረበዳ ባሉት ዱካዎችህ፤ በዳር አልባ ስፋት ውስጥ "እዚህ ነኝ፤ እዚህ ነኝ" በሚሉት የሕሩያንህ ቃላት፤ በግልጸትህ እስትንፋስና በክስተትህ የንጋት ልዝብ ነፋስ እማጠንሃለሁ።

ቀጥሎም ከሁሉም በላይ ታላቁን ስም ሦስት ጊዜ ይድገምና አጎንብሶ እጆቹን በጉልበቶቹ ላይ በማሳረፍ እንዲህ ይበል፡

አምላኬ ሆይ፤ አንተን እንዳስታውስና እንዳወድስህ ስለረዳኸኝ፤ እርሱን የምልክቶችህ ጎሕ የሆነውን ስላሳወቅኸኝ፤ በጌታነትህም ፊት እንድሰግድ ስለአደረግኸኝ፤ በአምላክነትህም ፊት ራሴን ዝቅ እንዳደርግና በታላቅነትህም አንደበት የተነገረውን ለመቀበል ስለአበቃኸኝ ምስጋና ለአንተ ይሁን።

ከዚያም ይቆምና እንዲህ ይበል፡

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ጀርባዬ በኃጢአቴ ክብደት ጎብጧል፤ ግዴለሽነቴም አውድሞኛል:: የእኔን ርኩስ ድርጊቶችና የአንተን ደግነት ባሰላሰልኩ ቁጥር ልቤ በውስጤ ይቀልጣል ፡ ደሜም በሥሮቼ ውስጥ ይፈላል:: በውበትህ አቤቱ አንተ የዓለም እሾት ሆይ! ፊቴን ወደ አንተ ለማቅናት እፍረት ይሰማኛል፤ ናፋቂ እጆቼም ወደ ቸርነትህ ሰማይ ለመዘርጋት ያፍራሉ:: አቤቱ አንተ የሰማዩና የምድሩ ዙፋን ጌታ የሆንክ አምላክ ሆይ! እንባዎቼ አንተን ከማስታወስና የአንተንም ባሕርያት ከማወደስ እንዴት እንዳገዱኝ እነሆ ታያለህ! አቤቱ አንተ የፍጡራን ሁሉ ጌታ፥ የሚታዩና የማይታዩ ነገሮች ሁሉ ንጉሥ የሆንከው ሆይ! ለተወዳጆችህ እንደልግስናህና እንደጸጋህ መጠን እንድ:ታደርግላቸው በመንግሥትህ ምልክቶችና በግዛትህ ምሥጢራት እማጠንሃለሁ::

ቀጥሎም ከሁሉም በላይ ታላቁን ስም ሦስቴ ይድገምና ተንበርክኮ ግንባሩን ወደ መሬት በመድፋት እንዲህ ይበል፡

አምላካችን ሆይ፡ ወደ አንተ የሚያቀርበንንና በመጻሕፍትህና በቅዱሳት ጽሑፎችህ ውስጥ ያሉትን መልካም ነገሮች የሚያድለንን ስለላክህልን ምስጋና ለአንተ ይሁን:: አቤቱ ጌታዬ ሆይ፡ ከዋጋ ቢስ ሃሳብና ከከንቱ አስተሳሰብ አጀቦች እንድትጠብቀን እንማጸንሃለን:: በእውነቱ አንተ ኃያሉ፡ ሁሉን አዋቂው ነህና::



ቀጥሎም ራሱን ቀና አድርጎ ይቀመጥና እንዲህ ይበል፡

አምላኬ ሆይ፡ ሕሩያንህ የመሠከሩትን እመሠክራለሁ ፡ የገነት አርያም ነዋሪዎችና በኃያሉ ዙፋንህ ዙሪያ የከበቡት ሁሉ ያረጋገጡትንም አረጋግጣለሁ:: አቤቱ የዓለማት ጌታ ሆይ፡ የሰማይና የምድር መንግሥታት የአንተ ናቸው::

126

በየዕለቱ በሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ አንዴ 95 ጊዜ የሚደገም::

" አላሁ-ኡ-አብሃ"

## ሐ) ልዩ ጸሎቶችና መልእክቶች

መልእክት ለአህመድ::

127

እርሱ ንጉሡ ፡ ሁሉን አዋቂው፡ ጠቢቡ ነው!

እነሆ የገነት ወፍ ከዘለዓለም ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ፡ በቅዱስና በጣም ዜማ፡ ለቅኖች የእግዚአብሔርን ቅርበት አስደሳች ዜና በማወጅ፡ በመለኮታዊ አንድነት አማኞችን ለጋስ ወዳለበት መንበር በመጥራት፡ በንጉሡ፡ ክብር በተመላው ፡ ወደር በሌለው አምላክ የተገለጸውን መልእክት ለተላቀቁት በማስታወቅ፡ ፍቁራንን ወደ ቅድስና መንበርና ወደዚህ አንጸባራቂ ውበት በመምራት ይዘምራል::

በእውነቱ ይህ ያ ከሁሉም በላይ ታላቁ ውበት፡ በመልእክተኞች መጻሕፍት ውስጥ የተነገረለት፡ በእርሱም እውነት ከሐሰት የሚለይበትና የማንኛውም ትእዛዝ ጥበብ የሚፈተንበት ነው:: በእውነቱ፡ እርሱ የተከበረውን፡ የኃያሉን፡ የታላቁን አምላክ ፍሬዎች የሚያፈራ የሕይወት ዛፍ ነው::

አህመድ ሆይ! በእውነቱ እርሱ አምላክ መሆኑንና ከእርሱም ከንጉሡ፡ ከጠባቂው፡ ወደር ከሌለው፡ ምንም ከማይሳነው በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ አንተ መስክር:: ያም እርሱ ዓሊ (ባብ) በተባለው ስም የላከው፡ ትእዛዙንም ሁላችን የምንፈጽመው፡ እውነተኛው ከአምላክ ነበር::

በል፡ ሕዝብ ሆይ፡ በባያን ውስጥ ክብር በተመላው፡ በጠቢቡ ለተደነገጉት ለአምላክ ሕግጋት ታዛዦች ሁኑ:: ብታውቁት ኖሮ በእውነቱ እርሱ የመልእክተኞች ንጉሥ፡ መጽሐፉም መጽሐፈ እናት ነው::

እነሆ የገነት ወፍ ከዚህ ወህኒ ቤት ጥሪውን እንዲህ ያሰማሃል:: እርሱ ይህን ግልጽ መልእክት ማስተላለፍ ብቻ ይኖርበታል:: ያልፈለገ ከዚህ ምክር ገለል ይበል፡ የፈለገ ደግሞ ወደ ጌታው መንገዱን ይምረጥ::

ሕዝብ ሆይ፡ እነዚህን ጥቅሶች ከካዳችሁ በምን ማስረጃ በአምላክ አመናችሁ? እናንተ የውሸት ስብስቦች ሆይ፡ ማስረጃችሁን አቅርቡ::

በእርሱ ነፍሴ እጁ ውስጥ ባለችው፡ አሁንም ሆነ ወደፊት ተባብረው ቢተጋገዙም ፡ ይህን ሊያደርጉ ከቶ አይቻላቸውም::

አህመድ ሆይ! በሌለሁበት ጊዜ ቸርነቴን አትርሳ:: ቀኖቼን በቀኖችህ፡ በዚህ ሩቅ ወህኒ ቤትም ሥቃዬንና ግዞቴን አስታውስ:: የጠላቶች ሠይፎች ጭፍጨፋ ቢያዘንቡብህና ሰማይትና ምድር በመላ ባንተ ላይ ቢነሡብህም እንኳ ልብህ እንዳይመነታ በፍቅሬ የጸናህ ሁን::

ለጠላቶቼ እንደ እሳት ነበልባል፡ ለተወዳጆቼ የዘለዓለም የሕይወት ጅረት ሁን፡ ከእነዚያ ከሚጠራጠሩትም አትሁን::

መንገዴን በመከተል ሥቃይ፡ ለእኔም ስትል ውርደት ቢደርስብህ አትጨነቅ::

በአምላክ፡ በአምላክህና በአባቶችህ ጌታ ተማመን:: ሰዎችም አምላክን በዓይኖቻቸው ከማየት፡

ዜማውንም በጆሮዎቻቸው ከመስማት ማስተዋል ስለተሳናቸው፡ በተሳሳተ እምነት መንገድ በመንከራተት ላይ ናቸውና:: አንተም እንደምትመለከተው እንደዚህ ሆነው አገኘናቸው::

ስለሆነም፡ ከንቱ አምልኮታቸው በእነርሱና በልቦቻቸው መካከል ግርዶሽ በመሆን ከተከበረው፥ ከታላቁ አምላክ መንገድ አርቆአቸዋል::

በእውነቱ ይህን ውበት የማይቀበል፥ ያለፉትንም መልእክተኞች በመላ ያልተቀበለና ከእምቅድመ ዓለም እስከ ዘለዓለም በአምላክ ላይ ትዕቢት የሚያሳይ መሆኑን አንተ በራስህ እርግጠኛ ሁን::

አህመድ ሆይ፥ ይህንን መልእክት በሚገባ እወቅ:: በቀናትህም አዚመው፥ ከዚያም ራስህን አትግታ:: በእውነቱ አምላክ ለዚያ ለሚያዜመው የመቶ ሰማዕታትን ዋጋና በሁለቱም ዓለማት ያለውን ግልጋሎት አዞለታልና:: ከእነዚያ ከአመስጋኞች ትሆን ዘንድ ፡ ከእኛ በኩል እንደቸርነት ከቅርበታችንም እንደምሕረት እነዚህን በረከቶች አድለንሃል::

በአምላክ! ማንም በሥቃይ ወይም በኃዘን ውስጥ ያለ ይህንን መልእክት በፍጹም ቅንነት ቢያነብ፡ አምላክ ኃዘኑን ያጠፋለታል፡ ችግሩን ይፈታለታል፡ ሥቃዩንም ያስወግድለታል::

በእውነቱ እርሱ መሐሪው፡ ሩኅሩኅ ነው:: ለዓለማት ሁሉ ጌታ፡ ለአምላክ ምስጋና ይሁን::



<u>መልእክተ እሳት::</u>

128

በስመ እግዚአብሔር፥ በፍጹም ጥንታዊው፥ በፍጹም ታላቁ::

በእውነቱ የቅኖች ልቦች በመለየት እሳት አለቁ:- የዓለማት ተወዳጅ ሆይ፥ የገጽታህ ብርሃን ማንጸባረቅ ወዴት ነው?

እነዚያ ለአንተ ቅርብ የሆኑት በብቸኝነት ጨለማ ውስጥ ተጥለዋል:- የዓለማት እሾት ሆይ፥ ከአንተ ጋር እንደገና የመገናኘት ንጋት ብርሃን ወዴት ነው?

የሕሩያንህ አካላት በሩቅ አሸዋዎች ላይ በመንቀጥቀጥ ላይ ናቸው:- የዓለማት አስደሳች ሆይ፥ የቅርበትህ ውቅያኖስ ወዴት ነው?

ናፋቂ እጆች ወደ ጸጋህና ወደ ቸርነትህ ሰማይ ተዘርግተዋል:- የዓለማት መልስ ሰጪ ሆይ፥ የስጦታህ ዝናቦች ወዴት ናቸው?

ያላመኑት በሁሉም ሥፍራ ለጭቆና ተነስተዋል:- የዓለማት ድል አድራጊ ሆይ፥ የሕግ ደንጋጊው ብዕርህ አስገዳጅ ኃይል ወዴት ነው?

ከሁሉም አቅጣጫ የውሾች ጩኸት ከፍ ያለ ሆኗል:- የዓለማት ቅጣት ሰጭ ሆይ፡ የኃያልነትህ ደን አንበሣ ወዴት ነው?

መላውን የሰው ዘር ቅዝቃዜ ጨብጦታል:- የዓለማት እሳት ሆይ፥ የፍቅርህ ሙቀት ወዴት ነው?

መከራ የመጨረሻ ከፍታው ላይ ደርሷል:- የዓለማት አዳኝ ሆይ፥ የእርዳታህ ምልክቶች ወዴት ናቸው?

አብዛኛዎቹን ሕዝቦች ጨለማ ከበባቸው፡ የዓለማት ብርሃን ጮራ ሆይ፡ የአሸብራቂነትህ ድምቀት ወዴት ነው?

የሰዎች አንገቶች ለተንኮል ተመዘዙ፡ የዓለማት አጥፊ ሆይ፡ የበቀልህ ሠይፎች ወዴት ናቸው?

ውርደት መጨረሻ አዘቅት ላይ ደርሷል፡ የዓለማት ክብር ሆይ፡ የክብርህ ዓርማዎች ወዴት ናቸው?

ፍጹም መሐረውን፡ ስምህን ገላጩን ኃዘኖች አስቆዩት፡- የዓለማት ደስታ ሆይ፡ የግልጸትህ ጎሕ ሐሴት ወዴት ነው?

የምድርን ሕዝቦች ሁሉ ጥልቅ ኃዘን ወረደባቸው፡ የዓለማት ሐሴት ሆይ፡ የደስተኝነትህ ዓርማዎች ወዴት ናቸው?

የምልክቶችህ ንጋት ሥፍራ በተንኮል ሃማቦች ተሸፍኖ ታያለህ፡- የዓለማት ኃይል ሆይ፡ የኃያልነትህ ጣቶች ወዴት ናቸው?

ኃይለኛ ጥማት ሰዎችን ሁሉ አሸነፈ፡- የዓለማት ምሕረት ሆይ፡ የቸርነትህ ጅረት ወዴት ነው?

ስግብግብነት የሰውን ዘር ሁሉ ምርኮኛ አደረገ፡- የዓለማት ጌታ ሆይ፡ ከዓለማዊ ነገሮች የመላቀቅ መገለጫዎች ወዴት ናቸው?

ይህን ግፍ የተዋለበትን በስደት ላይ ብቸኛ ሆኖ ታየዋለህ፡- የዓለማት ንጉሥ ሆይ፡ የትእዛዝህ ሰማይ ሠራዊቶች ወዴት ናቸው?

እኔ በባዕድ አገር ተጥያለሁ፡- የዓለማት ታማኝ ሆይ፡ የታማኝነትህ ዓርማዎች ወዴት ናቸው?



ጣረሞት በሁሉም ሰዎች ላይ ተጭኗል፡- የዓለማት ሕይወት ሆይ፡ የዘለዓለማዊ ሕይወት ውቅያኖስህ ሞገድ ወዴት ነው?

የሰይጣን ሹክሹክታ በእያንዳንዱ ፍጡር ላይ ተተንፍሷል፡- የዓለማት ብርሃን ሆይ፡ የእሳትህ ተወርዋሪ ኮከብ ወዴት ነው?

የብርቱ ስሜት ስካር አብዛኛውን የሰው ዘር አበላሸ፡- የዓለማት እሾት ሆይ፡ የንጽሕና ጎሕ የሆኑት ወዴት ናቸው?

ይህን ግፍ የተፈጸመበትን በሶሪያውያኖች መካከል በጭቆና ተሸፍኖ ታየዋለህ፡- የዓለማት ብርሃን ሆይ፡ እየነጋ ያለው የብርሃንህ ጮራ ወዴት ነው?

እንዳልናገር ተከልክዬ ታየኛለህ፡- የዓለማት ዘማሪ ወፍ ሆይ፡ እንግዲያውስ ዜማዎችህ ከወዴት ይመነጫሉ?

አብዛኛው ሕዝብ ከእውነት በራቀ ሐሳብና በከንቱ አስተሳሰብ ተሸፍኗል፡- የዓለማት መተማመኛ ሆይ፡ የእርግጠኝነትህ ምሳሌዎች ወዴት ናቸው?

ባሃ በመከራ ባሕር ውስጥ እየሰጠመ ነው፡- የዓለማት አዳኝ ሆይ፡ የአዳኝነትህ መርከብ ወዴት ናት?

የልሳንህን ጎሕ በፍጥረት ጨለማ ውስጥ ታየዋለህ፡- የዓለማት ብርሃን ሰጭ ሆይ፡ የጸጋህ ሰማይ ፀሐይ ወዴት ነው?

የእውነትና የንጽሕና ፡ የታመኝነትና የክብር መብራቶች ተዳፈኑ፡- ዓለማትን አንቀሳቃሽ ሆይ፡ የተበቃይ ቁጣህ ምልክቶች ወዴት ናቸው?

ማንንም የአንተን የራስህን ልዕልና ያሳወቀ

ወይም እርሱን በፍቅርህ መንገድ ምን እንደደረሰበት የሚያስላስለውን ለማየት ትችላለህን? የዓለማት ተወዳጅ ሆይ፡ አሁን ብዕሬ ይቆማል።

የመለኮታዊው ሌጥ ዛፍ ቅርንጫፎች በሚነጉደው የሰማ ፋንታ አውሎ ነፋስ ተሰባብረው ተጋድመዋል፡- የዓለማት አሸናፊ ሆይ፡ ከችግር የማውጣትህ ዓርማዎች ወዴት ናቸው?

ይህ ፊት በስም ማጥፋት አቧራ ተደብቋል፡- የዓለማት ምሕረት ሆይ፡ የርኅራኄህ ልዝብ ነፋሶች ወዴት ናቸው?

የቅድስና ካባ በቅጥፈት ሕዝብ ተበክሏል፡- የዓለማት አስዋቢ ሆይ፡ የብጽዕናህ መጎናጸፊያ ወዴት ነው?

የሰዎች እጆች ከፈጸሙአቸው ሥራዎች የተነሣ የጸጋ ባሕር ጸጥ አለ፡- የዓለማት እሾት ሆይ፡ የቸርነትህ ማዕበሎች ወዴት ናቸው?

ወደ መለኮታዊ ቅርበት የሚያመራው በር በጠላቶችህ ጭቆና ተቆልፏል፡- የዓለማት ቁልፍ ከፋች ሆይ፡ የስጦታህ መክፈቻ ቁልፍ ወዴት ነው?

ቅጠሎች በመራዥ የአመጽ ቅስቀሳ ነፋሶች ገረጡ፡- የዓለማት ለጋሽ ሆይ፡ የቸርነትህ ደመናዎች ዶፍ ወዴት ነው?

ሁለንተን ዓለም በኃጢአት አቧራ ጨለመ፡- የዓለማት ይቅር-ባይ ሆይ፡ የይቅር ባይነትህ ልዝብ ነፋሶች ወዴት ናቸው?

ይህ ወጣት በባድማ ምድር ብቸኛ ነው፡- የዓለማት ለጋሽ ሆይ፡ የመንግሥተ ሰማያዊው ጸጋህ ዝናብ ወዴት ነው?



ፍጹም ከፍተኛው ብዕር ሆይ፡ ከሁሉም በላይ ጣፋጭ የሆነውን ጥሪህን በዘለዓለማዊው ዓለም ሰምተናል፡- የዓለማት በደል የተፈጸመበት ሆይ፡ የታላቁ አንደበት ለሚናገረው ጅሮህን አቅና!

የዓለማት ተንታኝ ሆይ፡ ቅዝቃዜው ባይኖር ኖሮ፡ የቃላትህ ሙቀት እንዴት ይሰፍን ነበር?

የዓለማት ብርሃን ሆይ፡ መከራ ባይኖር ኖሮ የትዕግሥትህ ፀሐይ እንዴት ያበራ ነበር?

የዓለማት ትዕግሥት ሆይ፡ በክፉዎች ምክንያት አትማረር። የተፈጠርከው እንድትታገሥና እንድታሸንፍ ነው።

የዓለማት ፍቅር ሆይ፡ በቅዋሚ አነሳሾች መካከል፡ በቃል-ኪዳን አድማስ የአንተ መንጋትኛ እግዚአብሔርን የመናፈቅህ ሁኔታ እንዴት ጣፋጭ ነበር።

የዓለማት መንፈሳዊ ሐሴት ሆይ፡ በአንተ የነፃነት ሰንደቅ በከፍተኛው ተራራ ጫፍ ላይ ተተከለ፡ የቸርነትም ባሕር ተመመ።

የዓለማት ግዞተኛ ሆይ፡ ታገሥ። በብቸኝነትህ የአንድነት ፀሐይ አበራ፡ በመሰደድህም የአንድነት ምድር አጌጠ።

የዓለማት ኩራት ሆይ፡ ውርደትን የክብር አልባስ፡ መከራንም የመቅደስህ ማጌጫ አድርገናል።

አንተ የዓለማት ኃጢአት ሸፋኝ ሆይ፡ ልቦች በጥላቻ ተሞልተው ታያለህ፡ በይቅርታ ማለፉ ያንተ ነው።

የዓለማት መስዋዕት ሆይ፡ ሠይፎች ሲመዘዙ ወደፊት ተራመድ! ፍላጻዎችም ሲምዘገዘጉ ወደ ፊት ግፋ!

ለዓለማት ዋይታ መንስኤ የሆንከው ሆይ: አንተ ዋይታ ታሰማለህ ወይስ እኔ ዋይታ ላሰማ? ይልቁንም ለእምነትህ አሸናፊነት በሚጥሩት ብዛት ማነስ ምክንያት አለቅሳለሁ::

ንሁዱ ተወዳጅ ሆይ፡ በእውነቱ ጥሪህን ሰምቻለሁ፣ የዓለማት መሥራች ሆይ፡ አሁን የባሃ ፊት በመከራ ሙቀት፡ በሚያበራውም ቃልህ እሳት እየተንበለበለ ነው፣ ወደ ፈቃድህም እየተመለከተ በመስዋዕትነት ቦታ በታማኝነት ተነስቷል::

ዓሊ አክባር ሆይ፡ የታጋሽነቱን መዓዛ ልታሸትበት ለምትችልበትና የዓለማት ሁሉ ተወዳጅ በሆነው በእግዚአብሔር መንገድ የደረሰብንን ለምታውቅበት ለዚህ መልእክት ጌታህን አመስግን::

አገልጋዮች ሁሉ ይህን ቢያነቡና ቢያሰላስሉ ዓለማትን የሚያቀጣጥል እሳት በደም ሥሮቻቸው ውስጥ ይቀጣጠላል::

ረኀርሙ የፈውስ ጸሎት::

129

እርሱ ፈዋሹ፡ አርኪው ፡ ረዳቱ፡ ፍጹም ይቅር-ባዩ ፡ ፍጹም መሐሪው ነው::

አንተን እጠራለሁ አቤቱ የተከበረው ሆይ: ታማኙ ሆይ፡ ክብር የተመላው ሆይ! አንተ አርኪው፡



አንተ ፈዋሹ: አንተ ነዋሪው: አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ሉዓላዊው ሆይ: ከፍ አድራጊው ሆይ: ፈራጁ ሆይ! አንተ አርኪው: አንተ ፈዋሹ: አንተ ነዋሪው : አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ወደር የሌለው ሆይ: ዘለዓለማዊው ሆይ: አንድዬው ሆይ! አንተ አርኪው: አንተ ፈዋሹ: አንተ ነዋሪው: አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ከሁሉም በላይ የተወደሰው ሆይ: ቅዱሱ ሆይ: አጋዡ ሆይ: አንተ አርኪው : አንተ ፈዋሹ: አንተ ነዋሪው: አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ሁሉን አዋቂው ሆይ: ፍጹም ጠቢቡ ሆይ: ከሁሉም በላይ ታላቁ ሆይ! አንተ አርኪው: አንተ ፈዋሹ: አንተ ነዋሪው: አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ መሐሪው ሆይ: ግርማ የተመላው ሆይ: ደንጋጊው ሆይ! አንተ አርኪው: አንተ ፈዋሹ: አንተ ነዋሪው: አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ተወዳጁ ሆይ: ክቡሩ ሆይ: ከሁሉም በላይ ደስተኛው ሆይ! አንተ አርኪው: አንተ ፈዋሹ: አንተ ነዋሪው: አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ከሁሉም በላይ ኃያሉ ሆይ: አኑዋሪው ሆይ: ምንም የማይሳነው ሆይ! አንተ አርኪው : አንተ ፈዋሹ: አንተ ነዋሪው: አቤቱ አንተ

ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ገዥው ሆይ፡ በገዛ ራሱ ነዋሪው ሆይ፥ ሁሉን አዋቂው ሆይ! አንተ አርኪው አንተ ፈዋሹ ፥አንተ ነዋሪው ፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ መንፈስ ሆይ፥ ብርሃን ሆይ፥ ከሁሉ በላይ ግልጹ ሆይ! አንተ አርኪው፥ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ በሁሉ የምትዘወተረው ሆይ፥ አንተ በሁሉም የምትታወቀው ሆይ፡ አንተ ከሁሉም ሥውር የሆንከው ሆይ! አንተ አርኪው ፥ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ድብቁ ሆይ፥ ድል አድራጊው ሆይ፥ ለጋሱ ሆይ! አንተ አርኪው፥ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ፍጹም ኃያሉ ሆይ፡ ረዳቱ ሆይ፥ ሰዋሪው ሆይ! አንተ አርኪው፥ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው ፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ሠሪው ሆይ፥ አርኪው ሆይ፡ ነቃዩ ሆይ! አንተ አርኪው ፥ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አስነሺው ሆይ፡ ሰብሳቢው ሆይ፥ ከፍ አድራጊው ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ፍጹም የምታደርገው ሆይ፡ የማይገታው ሆይ፡ ጸጋ የተመላው ሆይ! አንተ



አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ቸሩ ሆይ፥ ከልካዩ ሆይ፡ ፈጣሪው ሆይ! አንተ አርኪው፥ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ ከሁሉም የላቀው ሆይ፥ አንተ ውቡ ሆይ፡ ለጋሱ ሆይ! አንተ አርኪው፥ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው ፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ ትክክለኛው ሆይ፥ ጸጋ የተመላው ሆይ፥ ለጋሱ ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ ሁሉን አስገዳጁ ሆይ፥ ዘላለም ነዋሪው ሆይ፥ ከሁሉም በላይ አዋቂው ሆይ! አንተ አርኪው፥ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ እጹብ ድንቁ ሆይ! የቀናት ቀደምቱ ሆይ፥ ቸሩ ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ የማይደፈረው ሆይ፡ የሐሴት ጌታ ሆይ፥ ተናፋቂው ሆይ! አንተ አርኪው፥ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ ለሁሉ ደጉ ሆይ፥ ለሁሉ ሩኅሩኁ ሆይ፥ ከሁሉም በላይ በጎ አድራጊው ሆይ! አንተ አርኪው፥ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው ፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ለሁሉ አለኝታ ሆይ፡ ለሁሉ መጠለያ ሆይ፡ ሁሉን ጠብቆ አኑዋሪው ሆይ! አንተ አርኪው ፡ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ የሁሉ ረዳት ሆይ፡ አንተ በሁሉም ተለማኙ ሆይ፡ ሕይወት ሰጪው ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ ፡ አንተ ነዋሪው ፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ገላጩ ሆይ፡ አፈራራሹ ሆይ፡ ከሁሉም በላይ መሐሪው ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው ፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ ነፍሴ ሆይ፡ አንተ የኔ ተወዳጅ ሆይ፡ አንተ እምነቴ ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ጥማትን አርኪው ሆይ፡ ከሁሉም የላቀው ጌታ ሆይ፡ ከሁሉ በላይ ብርቱ ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ ከሁሉ በላይ ታላቁ ትውስታ ሆይ፡ ከሁሉ በላይ ቅዱሱ ስም ሆይ፡ ከሁሉ በላይ ጥንታዊው መንገድ ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ ከሁሉም በላይ የተወደሰው ሆይ፡ ከሁሉም በላይ ቅዱሱ ሆይ! ብሩኩ



ሆይ! አንተ አርኪው፥ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አላቃቂው ሆይ፥ መካሪው ሆይ፡ አዳኙ ሆይ! አንተ አርኪው ፥ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ወዳጅ ሆይ፥ ሐኪም ሆይ፥ ማራኪው ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ክብር ሆይ፥ውበት ሆይ፥ ቸርነት የተመላው ሆይ! አንተ አርኪው አንተ ፈዋሹ፥ አንተ ነዋሪው፥ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ ከሁሉም በላይ የታመነው ሆይ፡ ከሁሉም ይበልጥ አፍቃሪው ሆይ፡ የንጋቱ ጌታ ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ለጋሹ ሆይ፡ ብሩህ አድራጊው ሆይ፡ ደስታ አምጪው ሆይ! አንተ አርኪው፥ አንተ ፈዋሹ፡አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ የበረከት ጌታ ሆይ! ከሁሉ በላይ ሩኅሩኁ ሆይ፡ ከሁሉም በላይ መሐሪው ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ የማይለወጠው ሆይ፡ ሕይወት ሰጪው ሆይ፡ የሕያው ሁሉ ምንጭ ሆይ! አንተ አርኪው፡ አንተ ፈዋሹ፡ አንተ ነዋሪው፡ አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ሁሉን ነገሮች ጠልቀህ የምታውቀው ሆይ: ሁሉን የምታየው አምላክ ሆይ: የልሳን ጌታ ሆይ! አንተ አርኪው: አንተ ፈዋሹ: አንተ ነዋሪው: አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ ግልጽ ሆኖም ሥውር: የማይታየው ሆኖም ታዋቂው ሆይ: በሁሉም የሚፈለገው ተመልካች ሆይ! አንተ አርኪው: አንተ ፈዋሹ: አንተ ነዋሪው: አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አንተን እጠራለሁ አቤቱ አንተ አፍቃሪዎችን የምትሰዋው ሆይ: ለክፉዎች የጸጋ አምላክ ሆይ!

አርኪው ሆይ: እጠራሃለሁ አርኪው ሆይ!

ፈዋሹ ሆይ: እጠራሃለሁ ፈዋሹ ሆይ!

ነዋሪው ሆይ: እጠራሃለሁ: ነዋሪው ሆይ!
አንተ ዘለዓለም ነዋሪው: አቤቱ አንተ ነዋሪው ሆይ!

አምላኬ ሆይ: አንተ የተቀደስክ ነህ! የልግስናህና የጸጋህ በሮች በሰፊው በተከፈቱበትና የቅድስናህ መቅደስ በዘለዓለም ዙፋን ላይ በተተከለበት ቸርነትህ: የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ወደ አንተ ልግሥናዎችና ስጦታዎች ገበታ በጠራህበት ምሕረትህ: ለዓላዊነትህና ታላቅነትህም ተገልጸ በቆመባት ሰዓትና የግዛትህ ኃያልነት እንዲገለጽ በተደረገባት የንጋት ጊዜ "አዎን" በሚለው ቃልህ በሰማይና በምድር በሚገኙት ሁሉ ፊንታ በገዛ ራስህ መልስ በሰጠህበት ጸጋህ እማጠንሃለሁ:: እንደገናም ይህን የተባረከውን መልእክት የያዘውን: የሚደግመውን: መልእክቱ ጋ የሚደርሰውንም: መልእክቱ በሚገኝበት ቤት አካባቢ



የሚያልፈውንም ሁሉ እንድትጠብቅ: በእነዚህ ከሁሉም በላይ ውብ በሆኑት ስሞች: በእነዚህ ከሁሉም በላይ የተከበሩና ከሁሉም በላይ የላቁ ባሕርያት: ከሁሉ በላይ በተከበረው ትውስታህ: በንጹሁና ምንም ጉድፍ በማይገኝበት ውበትህ: ከሁሉም በላይ ሕቡዕ በሆነው አዳራሽ ውስጥ በተደበቀው ብርሃንህና በእያንዳንዱ ንጋትና ምሽት የመከራን ካባ ባጠለቀው ስምህ እማጸንሃለሁ:: እንግዲህ በዚህ መልእክት አማካይነት: እያንዳንዱን ሕመምተኛ: በሽተኛውንና ምስኪኑን: ከእያንዳንዱ መከራና ጭንቀት: ከእያንዳንዱ አስከፊ ሥቃይና ኃዘን አንጻው: በዚሁ መልእክት: ወደ መመሪያህ መንገዶች: ወደ ይቅርባይነትህና ወደ ጸጋህም ጎዳናዎች ለመግባት የሚሻውን ማንኛውንም ሰው ምራው::

አንተ በእውነቱ ኃይል የተመላው: ፍጹም አርኪው: ፈዋሹ: ጠባቂው: ሰጪው: ሩኅሩኁ: ፍጹም ለጋሱ: ፍጹም መሐሪው ነህና ::

## የቅዱሱ መርከበኛ መልእክት

130

"እውነቱን ታውቁ ዘንድ የቅዱሱን መርከበኛ መልእክት አዋኙ: የተባረከው ውበት በመጪው ጊዜ ስለሚፈጸሙት ድርጊቶች ሙሉ በሙሉ እንደተነበየ አስተውሉ:: እነዚያ የሚያስተውሉት ጥንቃቄ ያድርጉ::"

እርሱ ጸጋ የተመላው: በጣም ተወዳጁ ነው!
ቅዱሱ መርከበኛ ሆይ!
የዘላለም መርከብህን በሰማይ ሠራዊት ፊት እንድትታይ እዘዛት:

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
በእርሱ ፡ ከሁሉም በላይ ድንቅ በሆነው ስም፡ በጥንቱ ባሕር ላይ እንሳፍፋት፡

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
ፍጹም ከፍተኛ በሆነው አምላክ ስም መልአካዊዎቹ መናፍስት እንዲሳፈሩአት አድርጋቸው።

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
ከዚያም፡ ምናልባት በውስጧ የሚኖሩት በዘላለማዊው ግዛት ወደሚገኘው ወደ ቅርበት መጠለያ ይደርሱ ዘንድ፡

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
በክብር ውቅያኖስ ላይ እንድትጓዝ፡ ከታሠረችበት እንድትለቀቅ አድርጋት።

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
ቀይማ ባሕሮች ዳርቻ ወደሆነው፡ ወደተቀደሰው ባሕር ዳርቻ ከደረሰች በኋላ፡

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
በውስጡ ጌታ በሞት-አልባ ዛፍ ውስጥ በውበቱ ነበልባል ወደታየበት ማዕከል፡

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
በውስጡ የእርሱ እምነት መገለጫዎች ራሳቸውን ከራስ ወዳድነትና ከምድራዊ ብርቱ ስሜት ወዳነጹበት፡

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
በዙሪያው የሙሴ ክብር ዘላለም ከሚኖረው ሠራዊት ጋር ወደሚዞረው፡

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
ከውስጡ የእግዚአብሔር እጅ ከታላቅነቱ ጉያ ወደተዘረጋበት፡



ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
ለነዋሪዎቹ ሁሉም መለኮታዊ ባሕርያት የተነገሩላቸው ቢሆንም፥ በውስጡ የእምነቱ መርከብ እንቅስቃሴ-አልባ ሆና ወዳለችበት ማዕከል፥

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
ከመርከቧ እንዲወርዱና ወደዚህ ወደማይታየው መንግሥተ-ሰማያዊ ማዕከል እንዲገቡ እዘዛቸው።

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
መርከበኛው ሆይ! ለእነዚያ በመርከቧ ውስጥ ለሚገኙት፥

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
ምናልባት እንደበረዶ ነጭ በሆነው በተቀደሰው ሥፍራ እንዳይዘገዩ፥

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
ይልቁንም ጌታ በዝቅተኞቹ ዓለማት ከመጠቀስ ሁሉ በላይ ወዳከበረው ማዕከል በመንፈስ ክንፎች ይበሩ ዘንድ፥

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
ልክ በዘላለማዊ የእንደገና መሰባሰብ ግዛት እንደሚገኙት የተመረጡ አዕዋፋት በህዋ ውስጥ ይከንፉ ዘንድ፤

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
በብርሃን ባሕሮች ውስጥ የተደበቁትን ምሥጢራት ያውቁ ዘንድ፥ በምሥጢራዊው መጋረጃ በስተኋላ እያለህ ያስተማርንህን አስተምራቸው።

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!
እነርሱ የምድራዊ ውስንነቶችን ደረጃዎች አልፈው የመለኮታዊ መርሖ ማዕከል ወደሆነው ወደ መለኮታዊ

አንድነቱ ደረጃ ደረሱ::

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

እነርሱ ወደዚያ÷ ጌታ ከእነርሱ ደረጃ በላይ እንዲሆን ወዳዘዘው ክብር ለመውጣት ተመኙ::

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

በዚያን ጊዜ የሚንበለበለው በራሪ ኮከብ ከእነዚያ በእርሱ ቅርበት መንግሥት ከሚኖሩት ውስጥ አውጥቶ ጣላቸው÷

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

እነርሱ በክብር ከፍታ ላይ ከሚገኘው ከማይታየው አዳራሽ በስተኋላ የታላቁ ድምጽ እንደሚከተለው ሲናገር ሰሙ:-

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"እናንተ ምግዚት መላእክት ሆይ!*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"የእነዚያ ለመረዳት የሚችሉት አዕምሮዎች ሊገነዘቡት የማይችሉት ከእውነት የራቀ እምነት መርከብ እንቅስቃሴ አልባ ሆና ወደቆመችበት አካባቢ:*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"የመንግሥተ ሰማያዊው እርግብ ክንፎች ደርሰውበት ከቶ ወደማያውቁት ከፍተኛ አካባቢ ለመውጣት አስበዋልና: በዝቅተኛው ዓለም ወደሚገኘው መኖሪያቸው መልሱአቸው::"*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

በዚህን ጊዜ የመንግሥተ-ሰማይዋ ድንግል ከተከበረው ማረፊያ ክፍሏ ውስጥ ሆና ወደውጭ ተመለከተች÷

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

በዓይኗም መንግሥተ-ሰማያዊ ሠራዊትን ጠቀሰች÷

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!



በገጽታዋ ብርሃን ሰማይንና ምድርን በማጥለቅለቅ÷

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

የውበቷም ብርሃን በትቢያ ሰዎች ላይ ሲያበራ÷

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

ሰዎች ሁሉ በሞት መቃብሮቻቸው ውስጥ ተንቀጠቀጡ::

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

ከዚያም እርሷ ከሁሉም እምቅድመ ዓለም ምንም ጆሮ ሰምቶት ከቶ የማያውቀውን ጥሪ አሰማች÷

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

እንደሚከተለውም አወጀች:- *"በእርሱ በጌታው! ያ እርሱ ልቡ: የተከበረውንና ክብር-የተመላውን አረባዊ ወጣት ፍቅር መዓዛ የሌለው:*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"በምንም ዓይነት ወደ ላቀው ከፍተኛ መንግሥተ-ሰማይ ክብር ለመውጣት አይችልም::"*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

ከዚህም በኋላ ከድንግል አገልጋዮቿ መካከል አንዷን ድንግል ወደ ራሷ ጠራች÷

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

እንዲህም በማለት አዘዘቻት:- *"ከዘላለም ቤተ-መንግሥቶች ወደ ህዋ ውረጂ:*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"እነርሱ በእጅጉ በጣም ውስጣዊ ልቦቻቸው ክፍል ውስጥ ወደደበቁአቸው ነገሮች ተመልከቺ::*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"የክፉዎች እጆች በአደረሱት ክፉ ድርጊት ምክንያት በብርሃን ቤተ-መቅደስ ውስጥ ተደብቆ የቆየውን የወጣቱን ካባ ሽቶ ከአሸተትሽ:*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"የዘላለማዊ ሀብት መገለጫዎች የሆኑት የገነት ክፍሎች ነዋሪዎች ሁሉ ይገነዘቡና ያጻምጡ ዘንድ፥*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"እነርሱ ሁላቸውም ከዘላለማዊ ክፍሎቻቸው ይወርዱና ይንቀጠቀጡ ዘንድ፡*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"ወደ ታማኝነት ከፍታዎች ለመምጠቃቸው ምስጋና እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ይስሙ ዘንድ፥*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"ምናልባት ከልብሶቻቸው የተወዳጁን መዓዛ ለማሽተት ይችሉ እንደሆን፡ በውስጥሽ ጩኸት አሰሚ።"*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

ከዚያም፥ ልክ ከወጣቱ ገጽታ ከሚች አካሉ በላይ እንደሚያበራው ብርሃን፡ የተወዳጁ ልጃገረድ ገጽታ ከመንግሥተ-ሰማያዊዎቹ ማረፊያ ክፍሎች አበራ፥

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

ከዚህም በኋላ ሰማያትንና በዚያ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉ በሚያበራው ዓይነት ከፍተኛ ማሽብረቅ ወደታች ወረደች።

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

እርሷ በመንቀሳቀስ በቅድስናና በታላቅነት ምድሮች ውስጥ በሚገኙት ነገሮች ሁሉ ላይ ሽቶ አርከፈከፈች።

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

በዚያ ስፍራ በደረሰች ጊዜ በፍጥረት የላቀ ማዕከላዊ እምብርት ወደ ሙሉ ከፍታዋ ላይ ደረሰች፥

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ በማያውቀውም ጊዜ



መዓዛቸውን ለማሽተት ፈለገች።

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

በውስጣቸው የፈለገችውን አላገኘችም፥ ይህም ፥ በእውነቱ፥ ከእርሱ ድንቅ ትረካዎች አንዱ ብቻ ነው።

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

ከዚያም በኋላ እርሷ በታላቅ ድምጽ ጮኸች፥ አለቀሰችና ከሁሉ በላይ ወደተከበረው ቤተ መንግሥቷ ውስጥ ወደ ራሷ ደረጃ ተመለሰች፥

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

ከዚያም በማስከተል በማር እንደበቷ ለብቻዋ በሹክሹክታ የተነገረ አንድ ምሥጢራዊ ቃል ተናገረች፥

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

በሰማይ ሠራዊትና ሞት-አልባ በሆኑት የመንግሥተ-ሰማይ ሴት አገልጋዮች መካከል የሚከተለውን ጥሪ አሰማች፡-

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*" በጌታው! ከእነዚህ ዓላማ ቢስ ይገባናል ባዮች የታማኝነትን ልዝብ ነፋስ አላገኘሁም!*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

*"በጌታው! ወጣቱ በግዞት ምድር ከእግዚአብሔር በራቁት ሰዎች እጆች ውስጥ ብቸኛና የተከፋ መሆኑን ቀጥሏል።"*

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

ቀጥሎም በውስጧ በጣም ከፍተኛ ጩኸት ስለአሰማች የሰማይ ሠራዊት ተንጫጫ፡ ተንቀጠቀጠም፥

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

እርሷም በአፏራ ላይ ወድቃ ሕይወቷን ሰጠች። የተጠራችና ወደ እርሱ ወደ ላይኛው ዓለም

ወደጠራትም ያዳመጠች ይመስላል::

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

በእርሱ የተከበረ ገነት እጅግ በጣም ውስጣዊ ማዕከል ውስጥ ከፍቅር ሀልውና እርሷን የፈጠረው የተወደሰ ይሁን!

ንዑዱ ጌታዬ የተወደሰ ይሁን!

ከዚህም ቀጥሎ የመንግሥተ- ሰማይ ሴት አገልጋዮች፡ በገጽታዎቻቸው ላይ በገነተ አርያም ውስጥ ነዋሪ የሆነ የማንም ዓይን እይታ አርፎበት ከቶ ከማያውቃቸው ማረፊያ ክፍሎቻቸው በፍጥነት ወጡ::

ከሁሉም በላይ ከፍተኛው ጌታችን የተወደሰ ይሁን!

እነርሱ ሁላቸውም በእርሷ ዙሪያ ተሰበሰቡ፡ እነሆም! አካሏን በትቢያ ላይ ወድቆ አገኙት፤

ከሁሉ በላይ ከፍተኛው ጌታችን የተወደሰ ይሁን! የእርሷን ሁኔታ እንደተመለከቱና በወጣቱ የተነገረውን ታሪክ አንድ ቃል እንደተገነዘቡ፥ ከእራሶቻቸው ጥምጥሞቻቸውን አወለቁ፥ መጎናጸፊያዎቻቸውን ቀደዱ፡ ፊቶቻቸውን ነጩ፥ ደስታቸውን ረሱ፡ እንባዎቻቸውን አፈሰሱ፥ በእጆቻቸውም ጉንጮቻቸውን ጠፈጠፉ፥ ይህም በእውነቱ፡ ከምሥጢራዊዎቹ አሳዛኝ ስቃዮች አንዱ ነው

ከሁሉም በላይ ከፍተኛው ጌታችን የተወደሰ ይሁን::



## የባሃኦላህ የጉብኝት መልእክት::

131

ይህ መልእክት በተለይ በባሃኦላህና በባብ መካነ መቃብር ላይ የሚደገም ነው:: እንዲሁም በመታሰቢያዎቻቸው ቀናት ያገለግላል::

አቤቱ አንተ የታላቅነት ክስተት ÷ የዘለዓለም ንጉሥና በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ ጌታ ሆይ! ከሁሉም በላይ ከተከበረው ሕልውናህ ጎሕ የቀደደው ምስጋና÷ ከሁሉም በላይ አንጸባራቂ ከሆነው ውበትህ ያበራው ክብር በአንተ ላይ ይረፍ! በአንተ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ገዥነቱ÷ የአምላክ ግርማና ታላቅነቱ የተገለጹ መሆናቸውንና የጥንታዊ ጮራ የቀን ከዋክብት በማይሻረው ትእዛዝህ ሰማይ ብርሃናቸውን መፈንጠቃቸውን ÷ ያልታየውም ውበት ከፍጥረት አድማስ በላይ ማብራቱን እመሠክራለሁ:: በብዕርህም እንቅስቃሴ ብቻ "ሁን" የሚለው ትእዛዝህ እንዲከበር መደረጉን÷ የተደበቀውም የአምላክ ምሥጢር መገለጹን÷ የተፈጠሩት ነገሮችም ሁሉ መፈጠራቸውን÷ ግልጸቶችም ሁሉ መገለጻቸውን እመሰክራለሁ::

ከዚህም በላይ÷ በአንተ ውበት የተወዳጁ ውበት መገለጹን÷ በገጽታህም የተናፈቀው ገጽታ ማብራቱን÷ ከአንተም በመነጨ አንድ ቃል ብቻ ለአንተ ታማኝ የሆኑት ወደ ከፍተኛው የክብር ጫፍ እንዲመጥቁ ÷ ከሐዲዎች ግን ወደ መጨረሻው ጥልቅ አዘቅት እንዲወርዱ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ መካከል መወሰንህን እመሠክራለሁ::

አንተን ያወቀ አምላክን ማወቁን፥ ወደ አንተ ዘንድ መቅረብን የተቀዳጀውም እግዚአብሔር ፊት የቀረበ መሆኑን እመሠክራለሁ። ስለዚህ በአንተና በምልክቶችህ ያመነ ፡ በሉዓላዊንትህም ፊት ራሱን ዝቅ ያደረገ፡ አንተንም የማየት ክብር ያገኘ፥ለፈቃድህም ታዛዥ የሆነ፡ በአንተም ዙሪያ የዞረ፥ በዙፋንህም ፊት የቆመ ቡሩኬው ታላቅ ነው። በአንተ ላይ በደል የፈጸመ ፡ አንተን የካደ፥ በምልክቶችህ ያላመነ፥ ሉዓላዊነትህን ያቃለለ፡ በአንተም ላይ ያመጸ፥ በአንተ ላይ እብሪተኛ የሆነ፡ ማስረጃዎችህን የተከራከረ፥ ከግዛትህና ከመንግሥትህ የሸሸ፡ አንተ ስሞቻቸውን ለይተህ በተቀደሱ መልእክቶችህ ላይ በትእዛዝህ ጣቶች ካሠፈርካቸው ከሐዲዎች ጋር የተቆጠረ ወዮለት።

አምላኬና ተወዳጄ ሆይ፥ እንግዲህ፥ ከራሴና ከዓለም አርቀው ወደ ቅርበትህና አንተ ወደምትገኝበት መንበሮች ያቀርቡኝ ዘንድ፥ ከምሕረትህና ከፍቅራዊ ደግነትህ ቀኝ እጅ የችሮታዎችህን ቅዱስ እስትንፋሶች አርብብብኝ። የሚያስደስትህን ለመፈጸም ኃይል አለህ። በእውነቱ አንተ በሁሉም ነገሮች ላይ የበላይ ነህ።

አንተ የእርሱ ውበት የሆንክ ሆይ! የእግዚአብሔር ምስጋናና አስታዋሽነት፥ የአምላክ ክብርና የእርሱ ግርማ በአንተ ላይ ይረፍ። የፍጥረት ዓይን እንደ አንተ በደል የደረሰበትን ፍጹም አይቶ እንደማያውቅ እመሠክራለሁ። የሕይወትህን ቀናት ሁሉ በሥቃይ ውቅያኖስ ውስጥ እንድትሰጥም



ተደርገሃል። በአንድ ወቅት በእግር ብረትና በሰንሰለት ታስረሃል፥ በሌላው ደግሞ የጠላቶችህ ሠይፍ ማስፈራሪያ ደርሶብሃል። ይህም ሁሉ ሆኖ ግን አንተ፥ በሁሉን አዋቂው፡ በፍጹም ጠቢቡ የታዘዝከውን ሰዎች ሁሉ እንዲያከብሩ አዘሃል።

ስለደረሰብህ በደሎች መንፈሴ መስዋዕት ይሁን፥ ስለተቀበልካቸውም መከራዎች ነፍሴ ቤዛ ትሁን። በአንተና በፍጡራንህ መካከል የተጋረደውን ግርዶሽ እንዲያስወግድ፥ የዚህኛውንና የመጪውንም ዓለም መልካም ነገር እንዲለግሰኝ፥ በአንተና በእነዚያ ፊቶቻቸው በገጽህ ብርሃን ድምቀት በበሩት፥ ለአንተም ፍቅር ሲሉ የታዘዙትን ሁሉ በፈጸሙት እግዚአብሔርን እማጸነዋለሁ። በእውነቱ አንተ ፍጹም ኃያሉ፥ ከሁሉም በላይ የተከበረው፥ ፍጹም ክብር የተመላው ፡ ዘለዓለም ይቅር-ባዩ፥ ከሁሉም በላይ ሩኅሩኅ ነህና።

ጌታ አምላኬ ሆይ፥ ከሁሉም በላይ የላቁት ስያሜዎችህ እስካሉና ከሁሉም በላይ የተከበሩት ባሕርያትህ እስከሚኖሩበት ጊዜ ድረስ፥ መለኮታዊውን የሎጥ ዛፍ ከነቅጠሎቹ፥ ከነቅርንጫፎቹ፥ ከነቀንበጦቹ፥ ከነግንዶቹ፥ ከነውልዶቹ ባርከው። እንግዲህ ከጠብ አጫሪው ተንኮልና ከጭቆና ሠራዊት ጠብቀው። በእውነቱ አንተ ፍጹም ኃያሉ፥ ከሁሉም በላይ ኃይል የተመላው ነህና። ጌታ አምላኬ ሆይ፥ ወደ አንተ የቀረቡትንም አገልጋዮችህንና ሴት አገልጋዮችህን ባርካቸው። አንተ በእውነቱ ፍጹም ለጋሱ፥ ጸጋው ወሰን የሌለው ነህና። ከአንተ ከዘለዓለም ይቅር-ባዩ፥ ከሁሉም በላይ ለጋሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም።

## የጥበቃ ጸሎት (መልእክት)

132

እጅግ በተከበረው፥ በፍጹም ከፍተኛው፡ ከሁሉም በላቀው፥ በእርሱ ስም!

ጌታ አምላኬ ሆይ፥ አንተ የተወደስክ ነህ! አቤቱ አንተ ጌታዬ፥ አምላኬ፥ ደጋፊዬ፥ አለኝታዬ፥ መጠጊያዬ፥ ብርሃኔም የሆንክ አምላኬ ሆይ! ይህን መልእክት የያዘውን ከማንኛውም መቅሰፍትና ቸነፈር፥ ከእያንዳንዱ ክፉ ወንድና ሴት፥ ከክፉ አድራጊዎች ክፋት፥ ከኢአማኒያንም ሴራ እንድትጠብቀው፡ ከአንተ ከራስህ በስተቀር ሌላ ማንም በማያውቀው በኀቡዑና በክቡሩ ስምህ እለምንሃለሁ:: ከዚህም በላይ፥ አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ አቤቱ አንተ የሁሉንም ነገሮች ግዛት በመዳፍህ ውስጥ የያዝከው ሆይ፥ ከማንኛውም ሕመምና ስቃይ ጠብቀው:: አንተ በእውነቱ በሁሉም ነገሮች ላይ ሙሉ ሥልጣን አለህ:: አንተ የፈቀድከውን ታደርጋለህ፥ ደስ ያለህንም ታዛለህና::

አቤቱ አንተ የነገሥታት ንጉሥ ሆይ! አቤቱ አንተ ቸር ጌታ ሆይ! አቤቱ አንተ የጥንታዊ በረከት ምንጭ ሆይ! አቤቱ አንተ የጸጋ፥ የልግስናና የስጦታ መፍለቂያ ሆይ! አቤቱ አንተ ሕመመተኞችን ፈዋሹ ሆይ! አቤቱ አንተ ፍላጎቶችን አርኪው ሆይ! አቤቱ አንተ የብርሃን ብርሃን ሆይ! አቤቱ አንተ ከብርሃናት ሁሉ በላይ ብርሃን ሆይ! አቤቱ አንተ እያንዳንዱን ክስተት ገላጩ ሆይ! አቤቱ አንተ ሩኅሩኁ ሆይ! አቤቱ



አንተ መሐሪው ሆይ! ከሁሉም በላይ ታላቅ በሆነው ምሕረትህና በተትረፈረፈው ጸጋህ ፡ ይህን መልእክት በያዘው ላይ ምሕረት ይኑርህ፥ አቤቱ አንተ ጸጋ የተመላው፥ በረከት የተመላው ሆይ! በተጨማሪም፥ ልቡና አዕምሮው ከሚጠሉት ከማንኛውም ነገር በተከላካይነትህ ጠብቀው:: በእውነቱ አንተ ከእነዚያ ኃይል ከተጎናጸፉት ሁሉ በላይ ኃይል የተመላው ነህ:: ከእርሱ፥ ከኃያሉ፥ ከሁሉ በላይ ከተወደደው በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ አምላክ ስለ ራሱ የመሠከረውን አንተም መሥክር:: አቤቱ አንተ እየወጣ ያለው ፀሐይ ሆይ፥ የእግዚአብሔር ክብር በአንተ ላይ ይረፍ!

## የዓመት ማማሚያ (የአያሚ-ሀ)ቀናት ጸሎት::

133

በባሃኢ ዘመን አቆጣጠር፡ በአሥራ ስምንተኛ ወርና የዓመቱ የመጨረሻና የጾም ወር በሆነው በአሥራ ዘጠነኛው የባሃኢ ወር መካከል ከየካቲት 19-22 እና በየአራት ዓመቱ ከየካቲት 18-22 ያሉትና አያሚ-ሀ (የሀ-ቀናት)በመባል የሚታወቁት ቀናት ለጾሙ ዝግጅት ማድረጊያ ፡ የመስተንግዶ ፡ ምጽዋትንና ስጦታዎችን መስጫ ቀናት መሆን አለባቸው::

አምላኬ ፡ እሳቴና ብርሃኔ ሆይ! አቤቱ አንተ የስሞች ንጉሥ የሆንክ ሆይ፡ አንተ በመጽሐፍህ ውስጥ አያሚ-ሀ (የሀ-ቀናት) ብለህ የሰየምካቸው ቀናት ተጀመሩ፥ ከሁሉም በላይ የተከበረው ብዕርህ በፍጥረትህ ዓለም የሚገኙት ሁሉ እንዲያከብሩት ያዘዘውም ጾም እየተቃረበ ነው:: ጌታዬ ሆይ፥ ለእያንዳንዱ ነፍስ በመንበርህ ግቢ ውስጥ ሥፍራ፥ በገጽህ ብርሃን ውበቶች ግልጸትም ዘንድ መቀመጫ

እንዲመደብለት እንድትፈቅድ፡ በእነዚህ ቀናት፡ እንዲሁም በእነዚያ በዚህ ወቅት በትእዛዛትህ ገመድ ላይ በተንጠላጠሉትና የሕግጋትህን እጄታ አጥብቀው በያዙት ሁሉ እማጸንሃለሁ::

ጌታዬ ሆይ: እነዚህ ምንም ዓይነት ብልሹ ዝንባሌ አንተ በመጽሐፍህ ከላይ ከላክኸው ያልከለከላቸው አገልጋዮችህ ናቸው:: እነርሱ በእምነትህ ፊት አንገታቸውን ደፍተዋል: መጽሐፍህንም ከአንተ ብቻ በሚገኘው ከፍተኛ ቆራጥነት ተቀብለዋል፡ የአዘዝካቸውንም አክብረዋል፡ በአንተ የተላከውንም ሁሉ ለመከተል መርጠዋል::

ጌታዬ ሆይ: አንተ በቅዱሳት መጻሕፍትህ ውስጥ የገለጽከውን ማንኛውንም ነገር እንዴት እንደተቀበሉና እንዳመኑ ታያለህ:: ጌታዬ ሆይ: ጸጋ ከተመላበት ሕያውነትህ እጆች የዘላለምህን ውሀዎች እንዲጠጡ ስጣቸው:: ስለዚህ ለዚያ ራሱን በቅርበትህ ውቅያኖስ ውስጥ ለአሰጠመውና፡ አንተን የማግኘትን ምርጥ ወይን-ጠጅ ለተቀዳጀው ሰው የታዘዘውን ካሣ መዝግብላቸው::

አቤቱ፡ አንተ የነገሥታት ንጉሥና ለእነዚያ ለተረገጡት አዛኝ የሆንከው ሆይ: የዚህን ዓለምና የመጪውን ዓለም መልካም ነገር እንድታዝላቸው እማጸንሃለሁ:: በተጨማሪም ከፍጡሮችህ መካከል ማንም ያላወቀውን መዝግብላቸው፡ ከእነዚያም በአንተ ዙሪያ ከዞሩትና በዓለማትህም እያንዳንዱ ዓለም በዙፋንህ ዙሪያ ከተንቀሳቀሱት ጋር ቁጠራቸው::

በእውነት፡ አንተ ፍጹም፡ኃያሉ፡ ሁሉንአዋቂው፡ ሁሉን ተረጂው ነህና::



<u>የጾም ጸሎት</u>::

134

ምስጋና ላንተ ይሁን÷ ጌታ አምላኬ ሆይ! ለእኔና አብረውኝ ላሉት ሁሉ÷ ከሁሉ በላይ ወደሆነው ክብርህ ሰማየ ሰማያት ለመምጠቅ የሚያስችለንንና ተጠራጣሪዎችን ወደ አንድነትህ መቅደስ ከመግባት ካገዱአቸው የጥርጣሬ ጉድፎች የሚያነጻንን እንድትልክልን÷ ጨለማው ወደ ብርሃን በተለወጠበት÷ የሚዘወተረው መቅደስ በተገነባበት÷ የጽሑፍ መልእክት በተገለጸበትና የተዘረጋው ብራና ሽፋኑ በተነሣበት በዚህ ግልጸት እማጠንሃለሁ::

ጌታዬ ሆይ÷ እኔ ያ የአፍቃሪ ደግነትህን ገመድ አጥብቄ የያዝኩ÷ በምሕረትህና በለጋስነትህ ጠርዝ ላይ የተንጠላጠልኩ ነኝ:: ለእኔና ለተወዳጆቼ የዚህኛውንና የመጪውን ዓለም መልካም ነገሮች ሁሉ እዘዝልን:: እንግዲህ ÷ ከፍጡሮችህ መካከል እጅግ በጣም ምርጥ ለሆኑት ካዘዝክላቸው ሕቡዕ ሥጦታዎች አድላቸው::

ጌታዬ ሆይ÷ እነዚህ ቀናት አገልጋዮችህ ጾም እንዲጾሙባቸው ያዘዝካቸው ናቸው:: ከአንተ በስተቀር ከሌሎች ነገሮች ሁሉ ራሱን አግልሎ ለአንተ ብቻ ሲል የጾመ የተባረከ ነው:: ጌታዬ ሆይ ÷ አንተን እንድንታዘዝና ሕግጋትህን እንድናከብር እርዳኝ ÷ እነርሱንም እርዳቸው:: አንተ በእውነቱ የመረጥከውን ለማድረግ ኃይል አለህና::

ከአንተ ከሁሉን አዋቂው÷ ከፍጹም ጠቢቡ በቀር ሌላ አምላክ የለም:: የዓለማት ሁሉ ጌታ ለሆነው ለእግዚአብሔር ምስጋና ሁሉ ይሁን::

## 135

አምላኬ ሆይ፥ ከቅርበትህ ከተማ በር አርቀህ እንዳትጥለኝና በፍጡሮችህ መካከል በጸጋህ ክስተቶች ላይ ያደረግሁአቸውን ተስፋዎች እንዳትቀጭብኝ፥ በኃያሉ ምልክትህና በሰዎች መካከል በጸጋህ መገለጽ እማጠንሃለሁ፡፡ አምላኬ ሆይ፥ ፍጹም ቅዱሱን፥ ፍጹም አንጸባራቂውን ፥ ፍጹም ኃያሉን ፥ ፍጹም ታላቁን ፥ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፥ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ፡፡

አምላኬ ሆይ፥ ሁልጊዜ ይበልጥ ወደ በርህ ደጀሰላም እንድታቀርበኝ፥ ከምሕረትህ ጥላና ከቸርነትህ አኅበር እንድርቅ እንዳታደርገኝ በፍጹም ጣፋጩ ድምፅህና ፍጹም በተከበረው ቃልህ እማጠንሃለሁ፡፡ አምላኬ ሆይ፥ ፍጹም ቅዱሱን ፥ ፍጹም አንጸባራቂውን፥ ፍጹም ኃያሉን፥ ፍጹም ታላቁን፥ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፥ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ፡፡

አምላኬ ሆይ፥ በመኅናጸፊያህ መዓዛ እንድትስበኝና የቃልህን ምርጥ የወይን ጠጅ እንድጠጣ እንድታደርገኝ፥ በአንጸባራቂው የግምባርህ ውበትና ከፍጹም ከፍተኛው አድማስ በሚያበራው የገጽህ ብርሃን ብሩህነት እማጠንሃለሁ፡፡



አምላኬ ሆይ፥ ፍጹም ቅዱሱን፥ ፍጹም አንጸባራቂውን፥ ፍጹም ኃያሉን፥ ፍጹም ታላቁን፥ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፥ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ፡፡

አምላኬ ሆይ፥ ወደ ኋላ ሳላፈገፍግ ወይም እነዚያ በምልክቶችህ ያፌዙትና ከፊትህም የዞሩት በሚያቀርቡአቸው ሃሳቦች ሳልደናቀፍ እምነትህን እንዳገለግል በጣም እንድታነሳሳኝ፥ ልክ ፍጹም የተከበረው ብዕርህ በፍጥረትህ መንግሥት ላይ የሥውር ትርጉሞች ልዩ መዓዛ እያፈሰሰ በጽላቶችህ ገጾች ላይ እንደሚንቀሳቀስ ሁሉ፥ በፊትህ ላይ በሚንቀሳቀሰው ፀጉርህ እማጠንሃለሁ፡፡ አምላኬ ሆይ፥ ፍጹም ቅዱሱን፥ ፍጹም አንጸባራቂውን፥ ፍጹም ኃያሉን፥ ፍጹም ታላቁን፥ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፥ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ፡፡

አምላኬ ሆይ፥ በውበትህ የቀኑ ኮከብ ላይ ለማተኮር እንድታስችለኝና የልሳንህንም የወይን ጠጅ እንድታድለኝ፥ የስሞች ንጉሥ በአደረግኸው፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በተመሰጡበት ስምህ እማጠንሃለሁ፡፡ አምላኬ ሆይ፥ ፍጹም ቅዱሱን፥ ፍጹም አንጸባራቂውን፥ ፍጹም ኃያሉን፥ ፍጹም ታላቁን፥ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፥ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም

ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ።

አምላኬ ሆይ፡ ፈቃድህ ያሻውንና ዓላማህ የከሰተውን እንዳደርግ በጸጋህ እንድትረዳኝ፥ ፍጹም ከፍተኛ የተራራ ጫፎች ላይ ባለው የግርማህ መቅደስና በፍጹም ከፍተኛ ኮረብታዎች ላይ ባለው የግልጸትህ አኀበር እማጠንሃለሁ። አምላኬ ሆይ፥ ፍጹም ቅዱሱን ፍጹም አንጸባራቂውን፡ ፍጹም ኃያሉን፥ ፍጹም ታላቁን፥ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፥ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ።

አምላኬ ሆይ፥ የእኔ ከሆነው ሁሉ እንድሞትና የአንተ ለሆነው ሁሉ እንድኖር እንድታድለኝ፡ ወዲያው ራሱን እንደገለጠ የውበት መንግሥት በማምለክ በሚያጎነበስለትና በመረዋ ዜማ በሚያወድሰው ውበትህ - ከዘለዓለም አድማስ ላይ በሚያበራው ውበትህ እማጠንሃለሁ። አምላኬ ሆይ፡ ፍጹም ቅዱሱን፡ ፍጹም አንጸባራቂውን፥ ፍጹም ኃያሉን፡ ፍጹም ታላቁን ፡ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፥ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ።

አምላኬ ሆይ፡ በፍጡሮችህ መካከል እንዳስታውስህና በሕዝቦችህም መካከል እንዳወድስህ እንድትረዳኝ፥ የፍቁራንህ ልቦች በነደዱለትና



በምድርም የሚኖሩት ሁሉ ነፍሶች በመጠቁበት በእጅግ በጣም ተወዳጁ ስምህ ክስተት እማጠንሃለሁ። አምላኬ ሆይ፡ ፍጹም ቅዱሱን፡ ፍጹም አንጸባራቂውን፥ ፍጹም ኃያሉን፡ ፍጹም ታላቁን፡ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፡ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ።

አምላኬ ሆይ፡ ፈቃድህ ከሚጠላው ከማንኛውም ነገር እንድታርቀኝና እርሱ የአንተ ምልክቶች ጎሕ የሆነው ወደ አበራበት ደረጃ እንድታቀርበኝ፡ በመለኮታዊው ሎጥ ዛፍ መንከሻከሽና በስሞችህ መንግሥት ውስጥ የልሳንህ ልዝብ ነፋሾች ድምጽ እማጠንሃለሁ። አምላኬ ሆይ፡ ፍጹም ቅዱሱን፡ ፍጹም አንጸባራቀውን፥ ፍጹም ኃያሉን፡ ፍጹም ታላቁን፡ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፥ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ።

አምላኬ ሆይ፥ በዕውቀትህ ማከማቻዎች ውስጥ የተደበቁትንና በጥበብህ ማስቀመጫዎች ውስጥ የተሸሸጉትን እንድትገልጥልኝ፥ በዚያ ከፈቃድህ አንደበት ከመውጣቱ ውቅያኖሶች እንዲተምሙ፡ ነፋሶችም እንዲነፍሱ፥ ፍሬዎችም እንዲገለጡ፡ ዛፎችም እንዲበቅሉ፡ ያለፉት ደብዛዎች ሁሉ እንዲጠፉ፥ ግርዶሾችም ሁሉ እንዲተረተሩ፥ ለአንተም ያደሩት ወደማይጨቆነው የእነርሱ ጌታ ገጽታ

ብርሃን እንዲገስግስ ባደረገው ፊደል እማጠንሃለሁ። አምላኬ ሆይ፡ ፍጹም ቅዱሱን ፡ ፍጹም አንጸባራቂውን፡ ፍጹም ኃያሉን፡ ፍጹም ታላቁን፡ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፡ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ።

አምላኬ ሆይ፡ በመጽሐፍህ ውስጥ አንተ ላወረድከውና በፈቃድህም ለተከሰተው ከበቂት ጋር እንድትቆጥረኝ፡ እንቅልፍን ከሕሩያንህና ከተወዳጆችህ ዓይኖች ባባረረው የፍቅርህ እሳት፡ ጎህ በሚቀድበትም ሰዓት በእነርሱ አንተን ማስታወስና ማወደስ እማጠንሃለሁ። አምላኬ ሆይ፡ ፍጹም ቅዱሱን ፡ ፍጹም አንጸባራቂውን፡ ፍጹም ኃያሉን፡ ፍጹም ታላቁን፡ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፡ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ።

አምላኬ ሆይ፡ ለታማኞችህና ለሕሩያንህ የጻፍከውን ለኔም ፍጹም በተከበረው ብዕርህ እንድትጽፍልኝ፡ ለአንተ የቀረቡት በትእዛዝህ ጦሮች መወጋትን እንዲቀበሉ፡ ለአንተ ያደሩትም የጠላቶችህን ሠይፎች በመንገድህ እንዲጋፈጡ ባደረጋቸው በገጽህ ብርሃን እማጠንሃለሁ። አምላኬ ሆይ፡ ፍጹም ቅዱሱን፡ ፍጹም አንጸባራቂውን፡ ፍጹም ኃያሉን፡ ፍጹም ታላቁን፡ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፡ በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት



ሁሉ በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ።

አምላኬ ሆይ፡ ወደ አንተ ለተመለሰው ለእያንዳንዱ ሰው፡ አንተ ያዘዝከውንም ጾም ላከበረው፡ በአንተ ፈቃድ ካልሆነ በቀር ለማይናገሩትና ያላቸውንም ሁሉ በአንተ መንገድና ለአንተ ፍቅር ሲሉ ለሰጡት ያዘዝከውን ካሳ እንድትጽፍለት፡ ያፍቃሪዎችህን ጥሪ፡ የእነዚያን አንተን የሚናፍቁትንም የኃዘን ድምፅ፡ እነዚያ ወደ ቅርበትህ ለመግባት የታደሉት የሚያሰሙትንም ጩኸት፡ እነዚያ ላንተ ያደሩት የሚያሰሙትንም ማቃሰት ባዳመጥህበትና በጸጋህና በቸርነትህ፡ የእነዚያን ተስፋቸውን በአንተ ላይ ያደረጉትን ሰዎች ምኞቶች በአሟላህበትና ፍላጎቶቻቸውንም በፈቀድክበት ስምህ፡ የይቅር ባይነትም ውቅያኖስ በፊትህ በተመመበትና የቸርነትህ ደመናዎች በአገልጋዮችህ ላይ በዘነቡበት ስምህ እማጠንሃለሁ።

ጌታዬ ሆይ፡ እነዚያ ሕግጋትህን አጥብቀው የያዙትና በመጽሐፍህ ውስጥ የደነገግህላቸውን ያከበሩት የፈጸሙትን በደል ትስርዝላቸው ዘንድ በአንተው በራስህ፡ በምልክቶችህ፡ በግልጽ መታወቂያዎችህ፡ በሚያበራው የውበትህ የቀኑ ኮከብ ብርሃንና በቅርንጫፎችህ እማጠንሃለሁ። አምላኬ ሆይ፡ ፍጹም ቅዱሱን፡ ፍጹም አንጸባራቂውን፡ ፍጹም ኃያሉን፡ ፍጹም ታላቁን፡ ፍጹም የተከበረውንና ፍጹም ክብር የተመላውን ስምህን እንደያዝኩ፡በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም ያሉት ሁሉ

በተንጠላጠሉበት የካባህ ዘርፍ ላይ ተንጠላጥዬ ታየኛለህ::

## የናውሩዝ (የዓዲስ ዓመት) ጸሎት::

136

ናውሩዝ መጋቢት 12 ቀን የባሃኢ ዓመት የመጀመሪያ ቀን፡ እንዲሁም የደስታና የመስተንግዶ ዕለት ነው::

አምላኬ ሆይ፡ ለአንተ ፍቅር ሲሉ አንተን ከሚያስከፉ ነገሮች ሁሉ ተጠብቀው ለጾሙት የናውሩዝን ክብረ በዓል ስለሰየምክላቸው ምስጋና ለአንተ ይሁን:: ጌታዬ ሆይ፡ የአንተ ፍቅር እሳትና አንተ ባዘዝከው ጾም የተፈጠረው ግለት በእምነትህ እንዲነዱ፡ አንተንም በማመስገንና በማስታወስ የተወሰኑ እንዲሆኑ እንዲያደርጋቸው ፈቃድህ ይሁን::

ጌታዬ ሆይ፡ አንተ ባዘዝከው ጾም ጌጥ እንዳስጌጥካቸው ሁሉ፡ በጸጋህና ልግስና በተመላበት ደግነትህ የተቀባይነትህንም ጌጥ አጎናጽፋቸው:: የሰዎች ሥራ ሁሉ ዋጋ የሚኖረው በአንተ መልካም ፈቃድ ሲደገፍ፡ በትእዛዝህም ላይ ሲመሠረት ነውና:: አንተ ጾሙን ያላከበረውን እንደጾመ ብትቆጥረው እንዲህ ያለው ሰው ከእነዚያ ከእምቅድመ ዓለም ጀምረው ጾሙን ከአከበሩት ጋር ይቆጠራል:: ጾሙን ያከበረውንም እንዳልጾመ ብትመለከተው፡ ያ ሰው የግልጾትህን ካባ በአቧራ እንዲቆሸሽ ከአደረጉትና ከዚህ ሕያው ምንጭ የጠራ ውሀ እንዲወገዱ ከተደረጉት ጋር ይቆጠራል::



አንተ ፡ በእርሱ፡ "በሥራዎችህ ሁሉ ምስጉን ነህ" የሚለው ዓርማ ከፍ የተደረገው፡ "ትእዛዝህ ሁሉ የሚከበር ነህ" የሚለውም ሰንደቅ በእርሱ አማካይነት የተዘረጋው ነህ:: የሁሉም ነገር ልቀት በትእዛዝህና በቃልህ ላይ ሲመሠረት ብቻ መሆኑን፡ የእያንዳንዱም ተግባር ዋጋ በአንተ ፈቃድና በፍላጎትህ መልካም ፈቃድ እንደሚወሰን እንዲገነዘቡ ፡ የሰዎችም ሥራዎች ሁሉ ልጓም በአንተ ፈቃድና በትእዛዝህ መዳፍ ውስጥ መሆኑን እንዲያውቁ ፡ ይህን ደረጃህን ለአገልጋዮችህ ግለጽላቸው:: ክርስቶስ፡- "*አንተ የመንፈሱ (የየሱስ) አባት ሆይ፡ ሥልጣን ሁሉ ያንተ ነው*" በማለት በሚያወድስባቸው፡ ወዳጅህም (መሐመድ) ፡- "*አንተ ከሁሉም በላይ ተወዳጅ የሆንከው ሆይ፡ ውበትህን ስለገለጽህ፡ ከእነዚያ ከአንተ በቀር ከሌላው ሁሉ ከተላቀቁት፡ ራሳቸውንም ወደ እርስ አንተን ራስህን ገላጭና የባሕርያትህ ክስተት ወደሆነው ከሥሩት በስተቀር ሌሎች ሰዎች ሁሉ እንዲያገኙ ወደ ተደረገበት ወደ ታላቁ ስምህ ግልጾት ዙፋን ለመድረስ የሚያስችላቸውን ለተወዳጆችህ ስለጻፍክላቸው ክብር ላንተ ይሁን፡*" በማለት በሚጮህባቸው በእነዚህ ቀናት ምንም ነገር ከውበትህ እንዳይጋርዳቸው ይህን እንዲያውቁ አድርጋቸው::

ጌታዬ ሆይ ፡ እርሱ የአንተ ቅርንጫፍ የሆነውና አጃቢዎችህ በሙሉ ፡ አንተን ለማስደሰት ባላቸው ጉጉት፡ በመንበርህ ክልል ውስጥ ሆነው ጾማቸውን ከጾሙ በኋላ ዛሬ ፈስከዋል:: ለእርሱም ለእነርሱም ፡ በእነዚያ ቀናት ወደ ቅርበትህ መድረክ ለገቡትም ሁሉ በመጽሐፍህ ውስጥ የወሰንከውን መልካም ነገር ሁሉ እዘዝላቸው:: እንግዲህ፡ በዚህም ሕይወት በወዲያኛውም ሕይወት የሚጠቅማቸውን አድላቸው::

አንተ በእውነቱ፡ ሁሉን አዋቂው፡ ፍጹም ጠቢቡ ነህና፡፡

## የአብዱል-ባሃ የጉብኝት ጸሎት፡፡

### 137

ይህ ጸሎት በአብዱል ባሃ መካነ መቃብር አጠገብ ይጸለያል፡፡ ለግል ጸሎትም ይሆናል፡፡ አብዱል-ባሃ እንዲህ ብሏል፦

*"ይህን ጸሎት በትሕትናና በኃለ ስሜት የሚያደርግ ማንም ሰው ፡ ለዚህ አገልጋይ ልብ ደስታንና ሐሴትን ያስገኛል፡፡ እንዲየውም እርሱን ፊት ለፊት እንደማግኘት ይቆጠራል፡፡"*

**እርሱ ንፁዱ ነው!**

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ዝቅተኛውና እንባዬን በማፍሰስ ላይ የምገኘው አገልጋይህ፡ ተማጻኝ እጆቼን ወዳንተ በማንሳት ፡ ከምሁራን ዕውቀትና ከአወዳሾችህ ውዳሴ ሁሉ በላቀው ደጀሰላምህ አፈራ ላይ ግንባሬን እደፋለሁ፡፡ በችሮታህ፡ ይህን በደጃፍህ ዝቅተኛ የሆነውን አገልጋይህን በምሕረትህ ዓይን ተመልከተው፡ በዘለዓለማዊውም የጸጋህ ውቅያኖስ ውስጥ አስጥመው፡፡

ጌታ ሆይ! እርሱ ምስኪንና ዝቅተኛ አገልጋይህ ነው፡ ተመስጦና አንተን እየተማጸነ፡ በእጅህ ውስጥ ያለ ምርኮኛ፡ ወዳንተ በጥልቅ ስሜት እየጸለየ፡ እምነቱን ባንተ ላይ በመጣል፡ በፊትህ እንባውን እያፈሰሰ፡ ወዳንተ እየተጣራ እንዲህ በማለት ይማጸንሃል፦



ጌታ አምላኬ ሆይ! ተወዳጆችህን አገለግል ዘንድ ጸጋህን ስጠኝ፡ ለአንተ አገልጋይ እንድሆን አበርታኝ፡ በቅድስና መንበርህ አንተን በማምለክና ለታላቅነት መንግሥትህ በመጸለይ ብርሃን ግንባሬን አብራው፡፡ በመንግሥተ ሰማያዊ መግቢያ በርህ ላይ እራሴን ከመውደድ የነጻሁ፡ በቅዱስ ክልልህም ውስጥ ከሁሉ ነገሮች የተላቀቅሁ እንድሆን እርዳኝ፡፡ ጌታ ሆይ! ከራስ ወዳድነት ከመራቅ ጽዋ እጠጣ ዘንድ ስጠኝ፡ በካባውም አልብሰኝ፡ በውቅያኖሱም ውስጥ አስጥመኝ፡፡ የፍጹም ክብር ጌታ ሆይ፡ በተወዳጆችህ መንገድ ላይ እንዳለው አፈራ አድርገኝ፡ በመንገድህ በምርጦችህ እርምጃዎች ለተቀደሰው አፈር ነፍሴን እንድሰዋ ፈቃድህ ይሁን፡፡

አገልጋይህ በማለዳና በውድቅት በዚህ ጸሎት ይጠራሃል፡፡ ጌታ ሆይ፡ የልቡን ምኞት አሟላለት! እምነትንህንና አገልጋዮችህን ያገለግል ዘንድ፡ ልቦናውን አብራለት፡ ልቡን አስደስትለት፡ ብርሃኑንም አቀጣጥልለት፡፡

አንተ ሰጪው፡ አዛኙ፡ ከሁሉም በላይ ለጋሱ፡ ጸጋ የተመላው፡ መሐሪው፡ ሩኅሩኁ ነህና!